# ነብር በቤታችን አለ!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ... ጠቦቶቼን ጠብቅ» (ዮሐ. 21:16)

የዕለቱ አገልጋይ በየዓመቱ ሁለት ጊዜ እየተሰባሰቡ በሚመክሩበትና የእግዚአብሔርን ቃል ከእግዚአብሔር ሰዎች በሚሰሙበት የመሪዎች ስብሰባ ላይ እንዲህ እያሉ መልእክታቸውን ማሰማት ጀመሩ:: «እኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ከሚፈልግብን ዋናና የመጀመሪያው ነገር የምንመራቸውን መንጎቻችንን /ሕዝቡን/ መንከባከብ፣ መመገብና መጠበቅ ነው:: በተለይም በዚህ ዘመን የበጎቻችንን መልክ ለይተን ማወቅ በሚገባን ጊዜ ላይ ነው ያለነው:: ምክንያቱም የበግ ለምድ ለብሰው ሾልከው የሚገቡ ተኩላዎች አሉ:: ቃላቸው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከሚያተኩር ይልቅ በጊዜያዊ ስሜት ላይ ብቻ አተኩሮ፣ በቃሉ ላይ ያልተመሠረቱ ስሜታውያንን በስሜት ኩርቻ ላይ አሳፍረው በመንዳት ከቤት የሚያስወጡ ሐሰተኞች ናቸው:: ትምህርታቸው የሥላሴን ማንነት የሚክድ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በማመን ብቻ የሚገኘውን የጸጋ ዘላለማዊ ደኅንነት በሰዎች ጥረትና ሥራ መዳን እንደሚቻል የሚለውጥ ጭድ የሌላው ጭቃ ነው:: ከእነዚህ ሐሰተኞች ራሳችንና ሕዝባችንን ለማዳን ቤተ ክርስቲያን ሕዝቧን በራሷ አገልጋዮች የበለጠ በመጠቀም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተና ሥር የሰደደ ትምህርት ማስተማር አለባት::» የሚለውን ትምህርታቸውን የበለጠ ለማስረዳት ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

ሁለት የተጣሉ ወንድማማቾች ማታ በጎች ከብቶች ወደ እየበረታቸውና ጋጣቸው ሲገቡ አንዱ ቆጥ ላይ አንዱ መደብ ላይ ሆነው ተኮራርፈው ይመለከታሉ:: ቆጥ ላይ ያለው ነብር ከእንስሳዎቹ ጋር አብሮ ተቀላቅሎ ሲገባ አይቷል:: እንዳይናገር ግን ተጣልተዋል:: ስለዚህ ዝም ተባብለው ጊዜው መሽቶ ሁሉም ተኙ:: ስለተጣሉ እንዱም ነብር እንቅልፍ እምቢ ብሏቸዋል:: ከቆጥ ላይ ያለው መደብ ላይ የተኛውን ወንድሙን ሲያዳምጠው ይወራጫል፤ ይቃኘዋል:: በዚህ ጊዜ በደረቁ ሌሊት በስሙ ወንድሙን ጠርቶ «ምን ሆነሃል? ቢለው፣ «በህልሜ ነብር በጫካ አይቼ ነው የምገላበጠው» አለው:: ቆጥ ላይ ያለው ወንድሙ ደግሞ፣ «ይኸው ነብር በጫካ ሳይሆን በቤታችን አለ» አለውና አረፈው::

አዎ፣ ዛሬም መንጋውን ሊያደሙና ሊበሉ መንፈሳዊ የመሰሉ ነብሮች ተመሳስለው በበጐች በረት አሉና ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል እውነቱን ከሐሰቱ፣ ምርቱን ከግርዱ ለይታ ልታወጣና መንጋዋን ልታድን፣ ልትጠብቅና ልትንከባከብ ይገባታል:: ይህንንም ለማድረግ ከብዛት ይልቅ ጥራት ላይ ማተኮር ይገባታልና ይህንን እንድታደርግ ጌታ ይርዳት:: አሜን::

ግጥምጥም:- እረኛው በጐቹን ካልለየ በቅጡ፣
ቤት ባዶ ይሆናል ተኩላዎች ካልወጡ::

2ኛ ጢሞ. 15:16
1ኛ ጴጥ. 2:1-21

## መንፈስ ቅዱስ የለም?

ሰባኪው፡ በሰንበት የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ለተሰበሰበው ሕዝብ እግዚአብሔር የሰጣቸውን መልእክት በከፍተኛ ድምፅ እንዲህ እያሉ መስበካቸውን ቀጠሉ።

«እዚህ የተሰበሰብን ሁላችን ዛሬ ወደዚህ የመጣነው ሁሉን ቻይ የሆነው ጌታ ያስተምረኛል፣ ይፈውሰኛል፣ ያጽናናኛል ብለን ነው። ይህ መልካም አሳብ ነው። እግዚአብሔር አለ ብሎ አምኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ነው። አንዳንዶች ዛሬ ከዚህ የራቀ አሳብ ይዘው ነው ያሉት። ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚሄዱት በራሳቸው መመዘኛ ምሪት ብቻ ነው። "እዚያኛው ቤተ ክርስቲያን ነው የምሄደው ምክንያቱም እዚያ መገለጥ ስለሚናገሩ፣ ልሳን ስለሚናገሩ፣ በሽተኛ ስለሚፈውሱ፣ የታወቁ ነቢያቶች ስላሉ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ስለሚካሄድ፣ አምልኳቸው በሰዓት ሳይገደብ የተለቀቀ ስለሆነ፣ አጋንንት እየተንጫጩ ስለሚወጣ..." እነዚህ ሁሉ ፈር በያዘ ሁኔታ ቢካሄዱ መልካም ናቸው። ነገር ግን እነዚህን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ስሙን በእውነት አምነው በሚጠሩት ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ አለና ባላችሁበት አባል በሆናችሁበት ቤተ ክርስቲያን ሆናችሁ ጠብቁት እንጂ የዘላን ኑሮ አትኑሩ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን አፏን ሞልታ ይህንን ያህል አባል አለኝ ለማለት የተቸገረችበት ዘመን ላይ ነው ያለነው። ለምን ቢባል ስሙን አስመዝግቦ ልቡን የሚነሳ ምእመን በዝቷልና ነው። እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ።» ለሚለው ምክር አዘል ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ።

ድንገት አንድ ቀን ክትትል ትምህርት የማስተምረው ተማሪዬ እንዲህ ሲል አስደንጋጭ ነገር ነገረኝ፣ «ሁለተኛ እዚህ ቤተ ክርስቲያን አልመጣም፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የለምና። ይኸው ሦስት ወር ሆነኝ፣ እስከአሁን በአምልኮ ላይ አጋንንት ጮኾ ሲወጣ አላየሁም። ሌላው ቤተ ክርስቲያን እየተንጫጫ ነው የሚወጣው።» አለኝ። በዚህ ጊዜ ራሴን ተቆጣጥሬ፣ «ወንድሜ፣ እውነቱ እንዲህ አይደለም። በአንድ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ የመኖሩ ምልክት የአጋንንት ጮኾ መውጣትና አለመውጣት አይደለም። ከፈለግክ ደግሞ ከሳምንት ጀምሮ ታያለህና ተስፋ ሳትቆርጥ ተመላለስ» አልኩትና ተለያየን። እኔም ለዚህ ሰው ጌታ በሚገባው መንገድ ራሱን እንዲገልጥለት፣ ቢቻል ወደ ቤተ

ክርስቲያን አጋንንት የሰፈረበት ሰው መጥቶ ጮኾ ሲያወጣ እንዳይ ጸለይኩ:: እግዚአብሔርም ታማኝ ነው:: ብዙም ሳይቆይ በሳምንቱ እርሱ ከተቀመጠበት ሁለተኛው ወንበር ላይ አጋንንት የያዘው ሰው ልክ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ሲጀመር ተነሣና ተፈጠፈጠ:: በጣም ደስ አለኝ:: ሰው ሁሉ «በኢየሱስ ስም» ሲል፣ እኔ፣ «ኢየሱስ ጌታ ነው» አልኩኝ:: ከአምልኮ መጨረሻ የክትትል ተማሪው ወደ እኔ መጥቶ፣ «በእውነት የእግዚአብሔር መንፈስ በዚህ ቤተ ክርስቲያንም አለ::» በማለት ንስሐ ገባ::

አዎ፣ እግዚአብሔር በእምነት በመጽናትና በተስፋ ለሚጠባበቁት በአሉበት ቦታ ተገልጦ ተአምራቱን ይሠራል፤ ጠላትንም ያሳፍራልና በአስቀመጠን ቦታ በፍቅር፣ በጸሎትና በታማኝነት እንድንጠብቀው ጌታ ሁላችንንም ይርዳን::

ጥቅስ:- «ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ» (ዮሐ. 14:14)

ግጥምጥም:- እግዚአብሔር በቦታ መቼ ይገደባል፣
መንፈሱና ስሙ በየትም ይሠራል::

| |
|---|
| 1ኛ ቆሮ. 15:58 |
| ኢሳ. 35:3-4 |

# ክፍል 7
# እግዚአብሔርን ስለመጠበቅ

## በክሰኛ አፍንጫውን ይሰበራል!

የቃል ጥናት ጥቅስ፥ «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ።» (ኤር. 29፡11)

ሰባኪው፥ «ብዙ ጊዜ ሰይጣን ባለንበት ሁኔታ እንድናጕረመርም እንጂ እንድናመሰግን አይፈቅድምና ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችንን ተጠቅሞ በብስጭት፥ በቁጣና በማጕረምረም ሕይወት ይሞላናል። ሆኖም አሁን ካለንበት ሁኔታ ወዲያ እግዚአብሔር የተሻለ ነገር እንዳዘጋጀ ማመንና ማወቅ ለሰይጣን የማያዳግም ምላሽ ነው። ማንኛውም ሰው ገባውም አልገባውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያለንበት ቦታ የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት የሥራ ቦታ ነው። እዚህ ያለነው ለሥራና ለተሻለ ነገር ነው። ይህንን የተረዳና ያመነ ክርስቲያን የጊዜውን መከራ ችሎ ከመከራው ባሻገር አምላኩ የሚሠራውን ድንቅ ሥራ በእምነት ሊጠባበቅ ይገባል። እግዚአብሔር ያያልና።» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንዲት ሰው ቤት የምትሠራ ሠራተኛ ነበረች። ከእምነቷ የተነሣ ብዙ መንከራተትና ሥራ ማጣት ቢደርስባትም በእምነቷ የጸናች ነበረች። እና ጌታም ለሥራ አንድ ጌታን ከማይወዱ አክራሪ ሰዎች ቤት ውስጥ ከተታት የምትጸልይበትም ስለአጣች ቤተሰቡ መተኛታቸውን ካረጋገጠች በኋላ ኩሽና አመድ ላይ ተንበርክካ ትጸልይ ነበር። በዚህ ጊዜ እመቤቷ ከመኝታ ቤታቸው ይሄዱና ጸጉሯን ይዘው፥ «ተነሽ፥ አንቺን ብሎ ጸላይ። ጴንጤ ደግሞ እቤቴ ገባ። ሁለተኛ ባገኝሽ አንቺን አያርገኝ» ብለው ሄዱ። ደነገጠች፥ «ተኝተው አልነበር እንዴ? እንዴት ሰሙኝ? ድምጼን ዝቅ አድርጌ ነገ እጸልያለሁ» አለች። አሁንም መጥተው አደናቀፉዋት። የመጨረሻም ማስጠንቀቂያ ሰጧት። እርሷም፥ «ሐናን የሰማ ጌታ እኔንም ይሰማኛል። በቃ አሁንም ድምጼን ሳላሰማ እጸልያለሁ» ብላ ስትወስን፥ የጌታ መንፈስ ምሥጢር ገለጠላት። ጉዳዩ ከድምጽ አይደለም። አንቺ ስትንበረከኪ በሴትዮዋ ውስጥ ያለው ሰይጣን ያውቃልና ስትሰሚ ገስጪ አላት። በደስታ ዘለለች። እንዲህም አለች፥ «ነገ ማታ የእኔ ጌታና የእሜቴ ጌታ ይዋጣላቸዋል።» እንዳለችውም በቀጣዩ ቀን ማታ አመዱ ላይ ተንበርክካ ስፍራ ወደማይወስነው ጌታ ስትጸልይ እሜቴ እንደለመዱት በሩን ከፍተው መጥተው ጸጉሯን ሊይዙ ሲሉ፥ «በኢየሱስ ስም» ስትል እሜቴ ወደቁ። ጸልያላቸው አጋንንቱ ለቅቋቸው ወደ አእምሮአቸው ሲመለሱ ያዩት ነገር የተገላቢጦሽ ሆነባቸው በ60 ብር የቀጠሯት ሠራተኛቸው በክብር ቆማ እሳቸው ሸቶ በጠገበው ቢጃማቸው አመድ ላይ ተንከባልለው ባዩ ጊዜ፥ ልጄ፥ ምን ሆኜ ነው?» አሉ። እርሷም፥ «ምን ያልሆኑት አለ» ብላ ሊገድላቸው ከነበረው አጋንንት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደፈወሳቸውና እርሱን ማመን እንዳለባቸው መናገር

ስትጀምር፥ እጁን ይዘው፥ «ነይ፥ ይህንን ያዳነኝን ጌታ ወንጌል አመድ ላይ አትነግሪኝም፥ ወደ ሳሎን ቤት እንሂድ» ብለዋት ሄዱ፥ ያመዱ ዘመን አበቃ።

አዎ፥ እግዚአብሔር የሚጎበኝበት ጊዜ አለው እና ባስቀመጠን ቦታ ሳናጉረመርም የፊታችንን ክብር እያየን እናገልግለው በከሰኛ አፍንጫውን ይሰበራል። በፊት ያለውን ክብሩን እያለመ የዛሬ ውበቱን ያጣል። በአሸናፊነትም ክብሩን ይጎናጸፋል። ክርስትናም እንዲሁ እንደሆነ እንድናስተውል ጌታ ይርዳን።

| |
|---|
| ኤር. 2፡2 |
| ኢሳ. 54፡4-5 |

ግጥምጥም:- ባስቀመጠን ቦታ ብንቆም ይሻላል፥

የጊዜው መከራ እንደ ጥላ ያልፋል።

# የሩቅ ሣር ለምለም መስሎ ይታያል

የቃል ጥናት ጥቅስ፦ «እርሱም አይዋሽም፤ ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው እርሱ አይዘገይም።» (እንባ. 2፡3)

ሰባኪው፥ «በዚህ ዘመን ሰይጣን የእኛን ሕይወት በምሳሌ ውስጥ የሚከተው እንዲህ እያለ ተስፋ በማስቆረጥ ነውና አትስሙት። ‹እግዚአብሔር ጸሎትሽን አይሰማም፥ የተስፋ ቃልሽንም አይፈጽምም፥ ትቶሻል፥ ትቶሃል። ይህንን አገር ለቅቀሽ ሂጂ› በማለት ነው። እግዚአብሔር በእውነት ማንንም አይተውምና ተስፋ አትቁረጡ፤ የዘገየው ለበጎ ነው። ለበለጠ ጥቅም (ክብር) ነው። የእኛ ነገር ይገደዋል፥ ደግሞ አንድ ልጁን የሰጠን ጌታ እንደ ፈቃዱ ከሆነው ምንም ነገር አያጎድልብንምና ተስፋ አንቁረጥ። ሥጋ፥ ዓለምና ሰይጣን በመተባበር የሚሰብኩንን ስብከታቸውን አንስማ። የሩቅ ሣር ለምለም መስሎ ይታያልና ጌታን እንጠብቅ። እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ ነውና በልባችን የምንመኘውን ለክብሩና ለጥቃማችን የሆነውን ያደርጋልና ተስፋ ሳንቆርጥ፥ የጠላትን ክስ ሳንሰማ በእምነት ጸንተን ልንጠብቀው ይገባል።» ለሚለው ስብከታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ፦

በግብርና የሚተዳደር አንድ ገበሬ ሁልጊዜ እንደዚህ የሚል ምኞት ነበረው። «መቼ ነው ይህች ላሜ ወልዳ ባለቤቴ ቂቤ የምትቀባው? ልጆቼ አጓት፥ አይብ፥ አሬራ፥ የሚጠጡት?» ይህንን ሁልጊዜ ያስባል፥ ያልማል፤ ነገር ግን ላሚቱ ልትወልድ አልቻለችም። መደበኛው የምትወልድበት ጊዜ አለፈ። አሁን ላሚቱ አሥር ወሯ ገብቷል። ሳትወልድ ስለዘገየችበት ገበሬው አዘነ፥ ከላይ የተመኘውም ምኞቱ ሁሉ ከንቱ መስሎ ታየው። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም በጊዜው ለበጎ አድርጎ ይለውጣልና ላሚቱ በጣም ደስ የምትል ሽንጉርጉር፥ ነጭ፥ ጥቁር፥ ቡናማ የተለያዩ ቀለማት በጥሩ የአቀማመጥ ሁኔታ ያላት ጥጃ ወለደች። በዚህ ጊዜ ገበሬው ምኞቱ ሁሉ በእግዚአብሔር ጊዜ እንደሆነለት አውቆ ለካ አምላኬ የዘገየው እያበጀ ነው።» ብሎ ተናገረ።

አዎ፥ ወገኖቼ፥ እግዚአብሔር የዘገየው ነገራችንን እያሳመረ፥ የበለጠ የተሻለ እኛ ከምናስበውና ከምንገምተው፥ ከምንጠብቀው በላይ ውብ እያደረገ እንጂ ሰይጣን እንደሚለው ረስቶን፥ ትቶን አይደለምና ተስፋ አንቁረጥ፤ ከምሬትና ከማጉረምረም ወጥተን በጊዜው የጊዜውን ሥራ በመሥራት እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭነውን ጌታ ብቻ እንድንጠብቅ ጌታ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም፡- ተስፋ እንዲህ መቁረጤ ከቶ ለምንድን ነው? | የሐዋ. 27፡25 |

የእኔ ጊዜ ቢያልፍም የእግዚአብሔር ገና ነው።

# ጠብቀነው ጠብቀነው

የቃል ጥናት ጥቅስ፦ «እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፥ አይደክሙም» (ኢሳ. 40፥30-31)

መጋቢው፥ «እግዚአብሔር ለሚጠብቁት በእውነት ታማኝ ነው። በጊዜውና በሰዓቱ ይደርሳል። አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን የተወጠና የረሳን ወይም የዘገየ የመሰለን ጊዜውን እየጠበቀ እንጂ ጌታ ልጆቹን ረስቶ አይደለምና በትዕግሥት እንጠብቀው። ልክ እንደ ቃሉ፥ «የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።» (ዕብ. 12፥2)። ቅዱሳን ሆይ፥ በፊቱ ስላለው ደስታ የሚለውን ልብ ብላችሁ አስተውሉ። ደስታ በፊታችሁ አለ ግን መታገሥን ይጠይቃል፤ ነውርን መናቅ ይጠይቃል፤ ሁሉን ቻዩን ጌታ ኢየሱስን ብቻ መመልከት ይጠይቃል፤ የነገሮቻችንን ፈጻሚና ራስ የሆነውን አምላክ በትዕግሥት መጠበቅ ይጠይቃል።» ለሚለው ገሩምና ድንቅ መልእክታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

የሕጻናት ሰንበት ትምህርት አስተማሪዋ እግዚአብሔርን ስለመጠበቅ በዕድሜያቸው ለጋ ለሆኑ ልጆች እንዲህ እያለች ታስተምራለች»። ልጆች፥ እግዚአብሔር በእምነት ለሚጠባበቁት ይደርሳልና ከተንኮልና ከክፋት እየራቃችሁ ጠብቁት» አለቻቸው። በዚህ ጊዜ አንዱ ልጅ እጁን አውጥቶ እንዲህ ሲል ጠየቀ። «ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ባይመጣ ምን እናድርግ?» መምህሯም እንዲህ ብላ መለሰች፥ «ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ ባይመጣ እንደገና ጠብቁት» አለቻቸው። በዚህ ጊዜ መልሱ ያላጠገበው ያ ሕጻን ልጅ እንደገና ጠየቀ ደስ በሚሉ አንደበቱ፥ «እኔ እኮ የምለው ቲቸር፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው ባይመጣስ ነው የምለው» አለ። መምህሯም መልሳ፥ «ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ ባይመጣ አሁንም ጠብቁት።»

አዎ፥ ወገኖች፥ ካቻምና ጠብቀነው፥ አምናም ጠብቀነው፥ ዘንድሮም ጠብቀነው አልመጣ ይሆን? በጉዳዮቻችን ላይ እግዚአብሔር ታማኝ ነው በጊዜው ይደርሳልና አሁንም ጠብቁ። ተስፋ አትቁረጡ። ባለመታከት የማይታክተውን ጌታ እንድንጠብቅ ከራሳችን እርምጃ ጌታ ይጠብቀን። አሜን!

ዘኁል. 23፥19
ኢሳ. 41፥13

ገጥምጥም፦ ተስፋ የሚታደሰው በተስፋ ነውና፥
አምላኬን ልጠብቅ ዛሬም እንደገና።

# እግዚአብሔር ጊዜ አለው

ሰባኪው፣ «ይዋል ይደር እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጐበኝበት የራሱ ጊዜና የራሱ መንገድ አለው። ስለዚህ የጌታን ጊዜና የጉብኝቱን መንገድ እንጠብቅ እንጂ አንችኩል። እግዚአብሔር አይዘገይም፣ ደግሞም አይቸኩልም፤ ግን የታቀደ የተወሰነ የራሱ ጊዜ አለው። አንዳንድ ጊዜ የዘገየ፣ ጠላታችንም ሊወርሰን ያለ ይመስለንና እንደ ሳኦል የራሳችንን እርምጃ እንወስዳለን፣ (1ኛ ሳሙ. 13:8)። 'ሳኦልም ሳሙኤል እንደቀጠረው ጊዜ ሰባት ቀን ቆየ ሳሙኤል ግን ወደ ጌልጌላ አልመጣም።' ይህ ግን እግዚአብሔር እመጣለሁ ብሎ ተናግሮ የቀረበት ሳይሆን ሰዓቱ እስኪሞላ የቆየበት ነው። ዛሬም የእግዚአብሔር ጊዜ ደርሶ ጽዋው እስኪሞላ እንጠብቅ እንጂ በዓለም፣ በሥጋና በሰይጣን ተገፋፍተን አንዳች ማድረግ የለብንም» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

«ሰፈሩ ሁሉ የሚሰግድለት አንድ ሀብታም ሰውና በተቃራኒው ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ የሆነበት አንድ ድሃ ሰው ነበሩ። ታዲያ አንድ ቀን ሀብታሙ ሰውዬ ሰው ሁሉ ሲሰግድላቸው የዚህ ድሃ ሰው አለመስገድ አበሳጭቷቸዋልና እንዲህ ብለው ጠየቁት። 'አንተ! ሰው ሁሉ ለእኔ ሲሰግድ አንተ ወድቀህ የማትሰግደው ለምንድን ነው?' ቢሉት፣ ለካ ድሃው አማኝ ኖሯልና 'ስግደት የሚገባው ለፈጣሪ ብቻ ነው፤ ሰው ለሰው እንዴት ይሰግዳል? ደግሞስ እኔና እርስዎ ምንድን ነው ልዩነታችን? እርስዎም አንድ እንጀራ ነው የሚበሉት እኔም አንድ እንጀራ ነው የምበላው' ሲል መለሰ። በዚህ ጊዜ ሀብታሙ 'ጉዳዩ ከእንጀራው ሳይሆን ከወጡ ነው። ለመሆኑ እንደ እኔ አራት ዓይነት ወጥ ትበላለህ?' ቢሉት፣ የእርሱ ወጥ ከአንድ አያልፍምና ዝም አለ። በዚህ ሁኔታ እየጸለየ ሳለ ያሉበት ሰፈ ግቢ ለንግድ ሥራ አመች ነበርና ለራሱ ትንሽ ቦታ ብቻ አስቀርቶ ለባለሀብቶች በብዙ ሺህ ብር ሸጠላቸው። አሁን ኑሮውም፣ ወጡም ተስተካከለና ያንን ሀብታሙን ጐረቤቱን ሰው አንድ ቀን መንገድ ላይ አግኝቶ 'ጌታዬ፣ የእርስዎ ወጥ አራት ዓይነት ነው አይደል? የእኔ አሁን ስድስት ገብቷል፤ እግዚአብሔር በጊዜው ከነወጡ ያበላል' አላቸው።»

አዎ፣ የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ አንገታችንን የደፋንበትን ነገር ይጐበኝና እኛም ቀና ብለን እንሄዳለን። በእውነት እግዚአብሔር ስለ ተስፋ ቃሉ ሲል አይዘገይምና ይህንን አስተውለን ከምንወስደው ሥጋዊ እርምጃችን ጌታ ይጠብቀን።

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «አላበጀህም፣ አምላክህ እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህም፤ ዛሬ እግዚአብሔር መንግሥትህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም አጽንቶልህ ነበር» (1ኛ ሳሙ. 13:13)።*

*ግጥምጥም:- እግዚአብሔር በጊዜው አውቃለሁ ይመጣል፣*
*ሳልቀድመው ታግሼ ልጠብቅ ይገባል።*

| |
|---|
| ዘፍጥ. 18:10፤ 21:1፤ መክ. 3:1 |

# ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም

የቃል ጥናት ጥቅስ: «አምላካችሁን እግዚአብሔርን ታመልኩታላችሁ እርሱም እህልንና ውኃህን ይባርካል፤ በሽታንም ከመካከልህ አርቃለሁ::»

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔርን በእውነትና በፍቅር ብናመልከውና ብንከተለው እኛን የሚያኖረን እግዚአብሔር ነው:: የዕለት እንጀራችንን የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው:: አንዳንዶች ከዚህ እውነት ርቀው ራሳቸውን በራሳቸው ለማኖር ምድዊ ብልጽግናን ለማትረፍ የራሳቸውን መንገድ ይጠቀማሉ:: የሌላውን እንጀራ በሐሰት በማጭበርበር ሲዘርፉና ሲያካብቱ በጥንቆላ፣ በአስማት፣ በሰላቢ፣ የአልጠግብ ባይነት ሥራ ሲሠሩና ሲያሠሩ ይታያሉ:: ጉቦ ሲበሉና ሲያመቻቹ ይውላሉ:: በቴሌቪዥን ግዙን ብለው ጥሩ ዕቃዎች አስተዋውቀው በግምባር ዋንኛው ሲመጣ መናኛውን ሲያቀርቡ ይገኛሉ:: በሐሰት ዘመናዊ ሐብትን ሊያግበሰብሱ ይሯሯጣሉ:: እውነቱ ግን ወዲህ ነው:: እግዚአብሔር ያልባረከው ብልጽግና ቋሚ ሳይሆን ጠፊ ነው፤ የሚያስከብር ሳይሆን የሚያዋርድ ነው፤ የሚያሳድግ ሳይሆን የሚጥል ነው፤ በልብ ደስታ የሚያኖር ሳይሆን በሕሊና ወቀሳ የሚያኖር ነው፤ በቅን መንገድ ሳይሆን በድጥ መንገድ የሚያስኬድ ነው:: ዛሬ አንዱ በሌላው እንጀራ ላይ አፈር እየጨመረ፣ ግማሹ ሲጠግብ ግማሹ ተርቦ ያድራል:: በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይሁን:: እግዚአብሔርን አምልኩት፤ እርሱ ያላችሁን እህል ውኃ ይባርክላችኋል::» ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

አንድ ሰው ለጓደኛው፣ በሕልሜ በሬ ሊወጋኝ ሲያሳድደኝ አደረ:: ላመልጠውም ቤት ብገባ አብሮኝ ይገባል፣ ባህር ውስጥም ብገባ እሳት ውስጥም ብገባ፣ ቤተ መንግሥትም ብገባ በሁሉም አብሮኝ ይገባል:: ይህ ምንድን ነው እባክህ?» ብሎ ቢጠይቀው፣ ጓደኛው፣ ጥያቄውን በጥያቄ ለመመለስ እንዲህ ይለው ጀመር፣ ብድር አለብህ?» «የለብኝም::» «ከሰው ጋር ተጣልተሃል?» «አልተጣላሁም::» «እሺ፣ ከመሥሪያ ቤት ሰውን በግፍ ከሥራው አባረሃል?» «አላባረርኩም::» «እሺ፣ የምትተኛው ምን ላይ ነው?» የጭድ ፍራሽ ላይ ሲለው ጓደኛው እንዲህ አለው፣ «በቃ ተወው፣ በሬው ታዲያ ምን ያድርግ? እንጀራው ላይ ተኝተህበት እኮ ነው የሚያሠቃይህ::» ብሎት አረፈው::

አዎ፣ መቼም ይህ ምሳሌ የሚያስቅ ቢመስልም ወደ ሰዎች ስንመልሰው ግን እውነትነት አለው። ዛሬ ዓለማችን እርስ በርሷ የምትበጣበጠው አንዱ በሌላው እንጀራ ላይ እየገባ፣ ራሱን አሳድጎ ሌላውን ለመጣል በሚያደርገው ትግል ነው። ወገኖች፣ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችን አምነን ብንከተለው እንጀራችንን /ኑሮአችንን/ እርሱ ይባርካል፣ ከዓለም መጨረሻ ሳይሆን ከዓለም መጀመሪያ ያደርገናል። እስቲ ቆም ብለን እናስብ። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የበላና ደስ ብሎት የሚኖር ማን ነው? ማንም የለም። የእኛን እንጀራ የሚባርክ እግዚአብሔር ነውና ከዚህ ክፉ አሳብ ተመልሰን ኑሮዬ ይበቃኛል ወደሚለው እግዚአብሔርን የማትረፊያ መንገድ እንድንመለስ ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም፡- «እንጀራ በእንጀራ እያነባበርኩኝ፣
በአሳብ ከመኖር ፈጽሞ ይቅርብኝ።

| |
|---|
| 1ኛ ጢሞ. 6:6 |
| 2ኛ ተሰ. 3:11፣ 12 |

# ክፍል 8

## እግዚአብሔን በሙሉ ኃይል ስለማገልገል

# የአሜሪካን ፕሬዚዳንት

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ::» (1ኛ ጴጥ. 5:4)

ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደተለመደው በዓመት ሁለት ጊዜ ባላት የአገልጋዮች የትምህርት ጊዜ ላይ መጋቢው እንዲህ እያሉ ማስተማር ቀጠሉ:: «እኛ አገልጋዮች ሙሉ ዋጋችንን የምንቀበለው ከምድር ወይም ከሰው ሳይሆን ከእረኞች አለቃ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነውና፤ እርሱን እያየን እናገልግል:: ደግሞ በዚህ ምድር ላይ የምናገኘው ነገር ሁሉ ያልፋልና፤ የማያልፈውን የክብር አክሊል ለማግኘት እንድከም:: በድካማችን ተገቢውን ክፍያ አለማግኘ ታችን ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም:: ለድካማችን በሕዝብ ዘንድ ክብር አለማግኘታችን ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም::ዛሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘ ነውን ክብርና ወደፊት ደግሞ የእረኞች አለቃ ሲገለጥ የምናገኘውን የማያልፈውን የዘላለም የክብር አክሊል እያሰብን በደስታ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳንል በታማኝነት ልናገለግለው ይገባል:: ይህንን ሳስብ አንድ የሰማሁትን ምሳሌ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ::»

በአንድ ሐገር ውስጥ ለ40 ዓመት በሚሽነሪነት ያገለገሉ ባልና ሚስት ነበሩ:: ታዲያ ከዚያ አገር አገልግሎታቸውን ፈጽመው ወደ አገራቸው አሜሪካ ሲመለሱ እነርሱ ሲያገለግሉ የቆዩበትን አገር በዕረፍታቸው ለአንድ ሳምንት ጎብኝተው የሚመለሱት የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ባሉበት መርከብ ነበር እየተመለሱ ያሉት:: ሀገራቸውም አሜሪካ ሲደርሱ የሀገሩ ሕዝብ ወጥቶ የተለያዩ መፈክሮች፣ ፊኛዎች ነጫጭ እርግቦች፣ አበባዎች፣ ይዘው በደስታ ጩኸት ፕሬዚዳንቱን ሲቀበሉ ሚሽነሪው አዩና በጣም አዝነው እንዲህ አሉ:- «እኔ ለ40 ዓመት እግዚአብሔርን አገልግዬ ነጩ ቆዳዬ በጥቁር ተበርዞ ሲመጣ ማንም የእቅፍ አበባ ይዞ አልተቀበለኝም:: እኚህ ፕሬዚዳንቱ ግን ለሳምንት ቆይተው ከዕረፍት ሲመለሱ ይኽ ሁሉ ክብር ጠበቃቸው::» በዚህ ጊዜ ባለቤታቸው፣ ይህንን አመለካከትህን ሳትቀይር ከዚህ መርከብ አንወጣም::» አሏቸው:: አብረውም ጸለዩ:: እግዚአብሔርም በመንፈሱ እንዲህ አላቸው:: ይህ የሚያልፍ ክብር ነው፣ የማያልፈውን የክብርን አክሊል እኔ እሰጣችኋለሁ::

አዎ፣ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆይ፣ የማያልፍ የክብር አክሊል ሊሰጠን ጌታ ታማኝ ነውና በሚያልፈው ክብር ተጠላልፈን እንዳንወድቅ እንጠንቀቅ:: የሚያልፈውን የዛሬውን ክብር እየናቅን የማያልፈውን ክብር ለማግኘት እንድንደክም ጌታ ይርዳን::

ግጥምጥም:- ለሚያልፈው ክብር ለምን እለፋለሁ፣
በቃ ከእንግዲህ ይቅርብኝ ብያለሁ::

2ኛ ጢሞ.4:6-8
መዝ.75:6

# የቄሳርን ለቄሳር

የቃል ጥናት ጥቅስ፡- «አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ ውደድ።» (ዘዳግ. 6:5)

ሰባኪው በዕለቱ ስለ መስጠት ለተሰበሰበው ሰው ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ፡- «እግዚአብሔር የተከፋ ልብ ሁለት አሳብ ያለውን አገልግሎትና አምልኮ አይፈልግም። አንድ እግራችንን በዓለም ሌላውን በቤተ ክርስቲያን አድርገን መመላለስ የለብንም። በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች የብዙ ነገር ሰዎች ሆነናል። እንዲያው ለደንቡ ቤተ ክርስቲያን መጥተን እንቀመጣለን እንጂ ለዚህች ለእግዚአብሔር ስጠተናታል ስምንላት የሦስት ሰዓት ጊዜ እንኳ ግማሹ አሳባችን (ልባችን) ውጪ ነው ያለው። በሥጋችን ጉባኤው መሐል ተቀምጠን፣ በልባችን ግን ወይ ስለ ቤታችን እናስባለን፣ ወይ ከሰዓት ስለሚኖረን የሠርግ ጥሪ፣ ወይ ከአምልኮ በኋላ ስለሚሰበሰበው ዕቁብ፣ ወይም ከአምልኮ በኋላ ከቤተሰባችን ወይም ከእጮኛችን ጋር ስለምናሳልፈው ጊዜ፣ ሌላም ሌላም እናስባለን። ይህ ሁሉ ባልከፋ ነበር። ነገር ግን አምልኳችን በግማሽ ልብና አሳብ መሆኑ እግዚአብሔርን እጅግ ያሳዝነዋልና ጌታን ስናመልክ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገን በጌታ ፊት መሆን ያስፈልጋል።» ለሚለው ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ።

የልጆች ሰንበት ትምህርት አስተማሪዋ ልጆችን የሰንበት ትምህርት እያስተማረች በዓይኗም ከእርሷ ጋር በሙሉ ልባቸው መሆናቸውን አለመሆናቸውን በዓይኗ ትከታተል ነበር። ታዲያ አንደኛው ልጅ በዓይኑ እርሷን ይመልከት እንጂ በሃሳቡ ከእርሷ ጋር እንደሌለ ገባትና። የምታስተምረውን ትምህርት ቆም አድርጋ ተማሪዎችን ጥያቄ ጠየቀች። «መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ስንት መጽሐፍት አሉት?» በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች ለመመለስ እጃቸውን አወጡ። እርሱም ምን እንደ ተባለ ሳይሰማ በግማሽ አሳቡ እጁን አብሮ አወጣ። አስተማሪዋም እራሱን፣ እሺ፣ አንተ መልስ» ስትለው፣ «የምስጋና ቀን ነው ለእኛ ዛሬ» ብሎአት አረፈ።

አዎ፣ ሁልጊዜ በግማሽ ልብ ከሆንን የእግዚአብሔር ነገር ያመልጠናል ሁለት አሳብ አንሁን። የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር እናድርግ እንጂ አናቀላቅል። ሁለት አሳብ ያለው ሁለት ጊዜ አይኖርም። በዚህ ምድር ላይ አንድ ጊዜ ብቻ ኖረን ነውና የምናልፈው በምንኖርበት ዘመን ሁሉ ጌታን በፍጹም ኃይላችን በፍጹም ልባችንና በፍጹም ነፍሳችን አምልከነውና አገልግለነው እንድናልፍ ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም፡- ልጄ ሆይ፣ ልብህን ሁሉ ስጥ እያለ፣
ግማሽ ልብ ሰጠሁት ሙሉ ሰጥቶኝ ሳለ።

ኢያሱ 14:8

# ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ቀነኒሳ

**የቃል ጥናት ጥቅስ፡- «ያገባሀልን ዕብራዊው ባሪያ ሊሣለቅብኝ ወደ እኔ ገባ፤ እኔም ድምጼን ከፍ አድርጌ ስጮኽ ልብሱን በእጄ ተወና ወደ ውጭ ሸሸ።» (ዘፍጥ. 39:17፣18)**

ሰባኪው፣ «ብዙ ጊዜ እንደተገነዘብኩትና ቃሉም እንደሚያረጋግጥልን በክርስትና ሕይወታችን የማሸነፊያው መንገድ እኛ ዝም ብለን ለጻድቅ ፈራጅ ጌታ እሳልፈን ስንሰጠው ነው። ዮሴፍ ይህንን ነው ያደረገው። ዮሴፍ ለጴጥፋራ ሚስት የሐሰት ክስ የመልስ መልስ ሲሰጥ አንመለከትም። የእውነት አምላክ በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ያለ ጌታ የመልስ መልሱን ሰጠለት። ለምንድን ነው ዛሬ በሕይወታችን ስልፍ የሚበዛብን፣ ከጉረቤት ከቤተ ክርስቲያንና ከመሥሪያ ቤት ሰዎች ጋር ሰላም ያጣነው? መልሱ ለጌታ ጊዜ ሳንሰጠው የመልስ መልሱን እኛ በለምንሰጥ ነው። በዚህ ዓለም ስንኖር የሚደግፉን እንዳሉ ሁሉ የሚነቅፉንም አሉ። ይህንን ካወቅን እንጉዳም። በክርስትና የሕይወት ሩጫ ውስጥ ሕዝቡ ሁሉ ይደግፈናል ማለት የለብንም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን እርግጠኞች ከሆንን ለእርሱ ዕድል ፈንታ እንስጠው እንጂ እንደ ሥጋችን ፈቃድ ለመጣብን እመልሰዋለሁ ብለን የመልስ መልስ ለመስጠት ቆም ብንል ሽንፈት ይገጥመናል። የእግዚአብሔርንም እጅ ሳናይ እንቀራለንና እንጠንቀቅ።» ለሚለው የአምላካዊ ቃል ምክር ቀጣዩን ምሳሌ አስረግጠው ተናገሩ፡-

ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ቀነኒሳ ሲሮጡ ደጋፊ እንዳላቸው ሁሉ ነቃፊም አላቸው። ደጋፊ እንዲህ ይል ይሆናል፡- «ኃይሌ በርታ! ጥሩ እንደተለመደው በዚህ በባዕድ ምድር የሐገራችንን ባንዲራ አውለብልብ።» ነቃፊዎች ደግሞ፣ «ኃይሌ ሁልጊዜ እያሸነፍክ ለመደነቅ ዘንድሮስ አትችልም። ፖል ቴርጋት ከኋላህ አለ።» ኃይሌ በዚህ ጊዜ ቆም ብሎ ለደጋፊው፣ «በደንብ እየጮሃችሁ ሞራል ስጡኝ፤» ለነቃፊውም፣ «ዛሬ እንደተለመደው አሸንፌ አሳያችኋለሁ» ቢል እስከአሁን ፖል ቴርጋት ሮጦ ሄዶ ያሸንፈው ነበር። ነገር ግን በሩጫ ሜዳ ላይ ኃይሌም ሆነ ቀነኒሳ፣ ሌሎችም ቆመው የመልስ መልስ አይሰጡም። የመልስ መልስ ከፊት ይገኛልና ሁሉም ከፊታቸው በትልቅ ቴሌቪዥን ያለውን ሰዓት ያያሉ፣ አሸንፈው የአገራቸው ስም በዓለም ሁሉ ሲከበር ያያሉ፣ ጨርሰው ሲመለሱ በአገራቸው የሚጠብቃቸውን የክብር አቀባበል ያያሉ። ስለዚህም የመልስ መልስ ሳይሰጡ ይሮጣሉ፣ ያሸንፋሉም።

አዎ፣ የእግዚአብሔር ቃል በዕብ. 12:2 ላይ፣ «የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፣ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ።» አዎን፣ ወገኖቼ፣ ጌታችንን ተመልክተን የመልስ መልሱን አቁመን ለቁጣው ዕድልና ፈንታ እየሰጠን የሕይወታችንን ሩጫ በትዕግሥት ብንሮጥ እናሸንፋለን እንጂ አንሸነፍም፣ እንወርሳለን እንጂ አንወረስም፣ እንደምቃለን እንጂ አንደበዝዝም። አሜን።

ግጥምጥም፡- የመልስ መልስ ሊሰጥ እግዚአብሔር ጊዜ አለው፣
እኔም ዝም ብዬ እስቲ እርሱኑ ልየው።

ዕብ. 12:1-3
ሮሜ 12:14-21

## ክፍል 9

## እግዚአብሔርን አምኖ ከሞት ስለ መዳን

# ሙሉ ወንጌልን እወዳለሁ

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» (ዮሐ. 3፥16)

ሰባኪው፥ ወደ ውጪ የምትሄድ የጎረቤታቸው ልጅ የሸኝት ፕሮግራም ላይ ተገኝተው እንዲህ እያሉ መልእክታቸውን ማቅረብ ጀመሩ። «ዛሬ የተሰበሰብነው ለምስጋና ነው። ግን ለመሆኑ የምናመሰግነው ማንን ነው? የምናመሰግነውስ ለምንድን ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጠን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይኸውም በመዝሙረ ዳዊት (136)፥1 ላይ፥ «እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና፥ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።» ይላል። እንግዲህ የምናመሰግነው እግዚአብሔርን የምናመሰግንበትም ዋና ምክንያት የዘላለም ምሕረትን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰጠንና ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት ስላሻገረን ነው። ዛሬ ይህንን ወንጌል ሰምታችሁ ያላመናችሁ ከሆነ የዘላለም ሞት ይጠብቃችኋልና አምልጡ፥ ወደ እግዚአብሔር ኑ። ልብ በሉ፥ እያልኩ ያለሁት ወደዚህኛው ቤተ ክርስቲያን ወይም ወደዚያኛው ቤተ ክርስቲያን ሂዱ ሳይሆን፥ ስለ እኛ ራሱን አሳልፎ በመስቀል ሞት ወደ ሰጠውና ሞትንም አሸንፎ በእግዚአብሔር ቀኝ ወዳለው ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። በእርሱ ታመኑ ነው እያልኩ ያለሁት። ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ መልካም ቢሆንም፥ የሄደ ሁሉ ከሞት የሚድነው እውነት፥ መንገድና ሕይወት ብቻ በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የታመነ እንደሆነ ነው። በዚህ ሙሉ ወንጌል ማመን የምትፈልጉ ብትኖሩ መጨረሻ ላይ አነጋግሩኝ። ብለው ጨረሱ።

በዚህ መልእክታቸው ጉባኤው ሁሉ ተነካ። በተለይም አንድ ሽማግሌ ሰባኪው በመጨረሻ አነጋግሩኝ ባሉት መሠረት ወደ ኋላ ቀርተው እንዲህ አሏቸው። ዛሬ ገና እውነተኛውን ወንጌል ሰማሁ፥ ሳትጨምር ሳትቀንስ በመስበክህ ደስ ብሎኛል። እኔ ሙሉ ወንጌልን እወዳለሁ። ከሁሉ በላይ የመጣህበትን ድርጅት ወይም ቤተ ክርስቲያን ሳትሰብክ ሙሉ ወንጌል በመስበክህ ደስ ብሎኛል። ከዘላለም ሞት የምድንበትን መንገድ ስፈላልግ ነበር ዘመኔን ሁሉ የኖርኩት። ዛሬ እግዚአብሔር በቃሉ ለልቤ ስለተናገረኝና መዳን በክርስቶስ ብቻ መሆኑም ስለገባኝ አሁን ጌታን አምናለሁና ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ?» ብለው ጠየቁ።

አዎ፥ ወገኖቼ ሆይ፥ ከዘላለም ሞት መዳን የሚቻለው በእግዚአብሔር ነው። መዳን በሌላ በማንም የለም። ከሰማይ በታች እንድንበትና እናመልጥበት ዘንድ የተሰጠን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና። አሁኑኑ በእርሱ እንመን። እኛም አገልጋዮች እግዚአብሔር በከፈተልን አጋጣሚ ሁሉ የሰውን ልብ የሚለውጠውንና ከሞትም መዳን በጌታ ብቻ መሆኑን የሚናገረውን ሙሉውን ወንጌል እንድናስተምር አምላክ በጥበቡ ያግዘን። አሜን!

ግጥምጥም፦ ሞትን ያሸነፈ ኢየሱስ እያለህ፥
ከሚሞት አምላክ ጋር ለምን ትሞታለህ?

| |
|---|
| ሮሜ 1፥16 |
| ቲቶ 2፥11–14 |

# የአስቄዋ ልጆች

የቃል ጥናት ጥቅስ፥ «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።» (ራእይ. 3፡20)

በጣም ድምጻቸውን ከፍ የሚያደርጉት በተለይ «እምነት የግል ነው» የሚለው አሳብ ላይ ነው። ምክንያቱም በቦታው የተሰበሰቡት አብዛኛው ወጣቶች በክርስቲያን ቤተሰቦቻቸው እምነትና ስም እንጂ በግላቸው ጌታን ተቀብለውና አምነው በእርግጥ አምላክ መሆኑን ተረድተው አልነበረም የሚመላለሱትና የሚያገለግሉት። ስለዚህም ሰባኪው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ጮኹ። «ወጣቶች በክርስቶስ መታመን የግል ነው። እንዳችሁም በቤተሰቦቻችሁ እምነት ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደማትገቡ ዛሬ እወቁ። የእናንተ የራሳችሁ ስም በሕይወት መጽሐፍ ላይ መጻፍ አለበት። ይህ የሚሆነው ደግሞ ጌታ ጌታ መሆኑን አውቃችሁ ስትታመኑትና እንደ ቃሉ በጽድቅ ኑሮ ስትመላለሱ ነው። ያን ጊዜ እግዚአብሔር ይከብራል፤ እናንተም ትድናላችሁ፤ ሰይጣንም ያፍራል። ይህም ደግሞ በምድር ሁሉ የታወቀ ይሆናል። ይህ ካልሆነ ግን የአስቄዋ ልጆች ዕጣ ይደርስባችኋል።» ብለው ስለ አስቄዋ ልጆች ከሐዋ. 19፡11-20 ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩ። «በጊዜው በእርሱ በታመነው ባሪያው በጳውሎስ እግዚአብሔር ድንቅ ተአምር ያደርግ ነበር። ከአካሉ ጨርቅ ወስደው በድውዮች ላይ ሲያደርጉ በሽታ ይለቅቃቸው፥ መናፍስትም ይወጡ ነበርና ይህንን የሰሙ የካህናት አለቃ የሆነው የአስቄዋ ሰባት ልጆች በከተማው ሰይጣን የያዘው ሰው ፈለጉና ጨርቅ በራሱ ላይ አድርገው፥ ‹ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ እናዝዛችኋለን፥ ውጡ› ይሉ ነበር። በዚህ ጊዜ አጋንንቱ ኢየሱስን በግላቸው ጌታቸው መሆኑን እንዳላመኑ አውቆ እንዲህ አላቸው፥ ‹ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ፥ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ። አሁን እኔ ግራ የገባኝ እናንተ እነማን ናችሁ?› ብሎ ዘሎ ተነሣና ልብሳቸውን ቀድዶ፥ አካላቸውንም አቆሳስሎ ሰባቱንም ከእናታቸው ሆድ እንደወጡ እራቁታቸውን አድርጎ አባረራቸው።» አሉና፥ አሁንም ጮክ ብለው፥ «የእነዚህ ልጆች አባት የካህናት አለቃ ነው፤ ያ ግን ለእነርሱ አልጠቀማቸውም። ስለዚህ በግላችሁ ጌታን የእኔ ጌታ ነው ብላችሁ ካላመናችሁ በስተቀር የቅዱሳን ቤተሰቦቻችሁ እምነትና በአፋችሁ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ነኝ ማለታችሁ ብቻውን በቂ አይደለም።»

አዎ፥ ክርስትና ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ደግሞ በመስቀል ላይ ደሙን ያፈሰሰው ለእያንዳንዳችን ነው። ስለሆነም የእያንዳንዳችንን ልብ ከፍተን በእውነት ይህንን ጌታ ዛሬውኑ ልናምንና የዘላለምን ሕይወት ልንቀበል ያስፈልጋል። ይህንን ወንጌል አምነንና የጌታንም ድምጽ ሰምተን ራሳችንን ለጌታ እንድናስረክብ እርሱ ይርዳን።

ማጥምጥም:- እምነት የግል ነው፥ አገር የጋራ ነው፤
ምክንያትህን ትተህ ሕይወትህን ስጠው::

2ኛ ጢሞ. 3፡14-15
ቆላ. 3፡17

# ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት

ሰባኪው፣ «በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ብዙ ነገሮች የመጀመሪያውን የልባችንን ዙፋን መውሰድ ቢፈልጉም መስጠት ግን የለብንም:: በሁሉም አቅጣጫ በሕይወታችን ቀድሚያው ቦታ ለክርስቶስ ብቻ ሊሆን ይገባል:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ግን በዚህች የክርስቲያን ደሴት እየተባለች በምትጠራው አገራችን የተገላቢጦሽ ሆኖ እናገኘዋለን:: እንደ ስማችን አይደለም ሥራችን፣ ቅድሚያ የምንሰጠው ለጣዖት፣ ለአድባር፣ ለጠንቋይ፣ በአጠቃላይ ለራሳችን ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ደግሞ ኪሳራን ያመጣል:: ለፈጣሪ ቅድሚያ መስጠት ሲገባን፣ ለፈጠረው ነገር ቅድሚያ ከሰጠን እግዚአብሔር በእኛ ላይ እንዲበቀል በቅንዓት እያነሣሣን ነው:: ስለዚህ በቀረልን ዘመን መገዛት፣ ክብር፣ ውዳሴ፣ ገናንት፣ አድናቆት ሁሉ ከዘላለም ሞት ላዳነን ጌታ ብቻ ልንሰጥና ልናሰጥ ይገባል» ለሚለው ጥልቅ ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

«ሁለት ጓደኛሞች በአንደኛው ቤት ምሳ እየበሉ ሳለ አንደኛው ጓደኛ ሁሌም የጓደኛውን ቤት ይወደዋልና ዙሪያ ገባውን እየተመለከተ ማድነቅ ጀመረ:: የተሰቀሉትን የአገር ባህል ዕቃዎችና ሥዕሎች ጭምር ሲመለከት በድንገት በተለምዶ «ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርት ጋር የመጨረሻውን ራት ሲበላ» ብለን የምንጠራውን ሥዕል ተመለከተና ማድነቅ ጀመረ::<አቤት፣ ደቀ መዛሙርቱ እንዴት ደስ ይላሉ! አቤት፣ በራሳቸው ላይ ያለው ክብ ነገር እንዴት ደስ ይላል! አቤት፣ የሚጠጡበት ዋንጫ እንዴት ደስ ይላል! አቤት፣ የለበሱት ልብስና የእግር መታጠቢያው ሳህን እንዴት ደስ ይላል!> እያለ ማድነቁን በቀጠለ ጊዜ፣ ጓደኛው እስከአሁን ያነሣቸው ወይም የሚደነቅባቸው በሙሉ ለዘላለም ሕይወት ማግኘት አንዳቸውም ዋጋ አለመክፈላቸውን ያለማወቁ አሳዝኖት እንዲህ አለው: «እባክህ ዙሪያ ዙሪያውን ከመኼድ የሰው ልጆችን ሁሉ ለማዳን በቀራኒዮ መስቀል ላይ ሞትን ድል ያደረገውን ጌታ ኢየሱስን ብቻ ተመልከት፣ እርሱንም አድንቅ» አለው::

አዎ፣ ዛሬስ እኛ ቅድሚያ ሰጥተን የምናደንቃቸውና የምንገዛላቸው ነገሮች ምን ይሆኑ? ቅድሚያውን ቦታና ክብር ለጌታ ስጡ:: እርሱ ብቻ የበላይ ነው:: በእውነት ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ተብላ የምትጠራው ከዝሙቷ፣ ከጥንቆላዋ፣ ከአስማቷ እና ከጣዖቷ ፈጽሞ ርቃ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔርን የበላይ ስታደርግ ብቻ ነው::

የቃል ጥናት ጥቅስ: «...እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፣ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም::» (ኢሳ. 44:6)

| |
|---|
| ኢሳ. 4:4-17<br>ሮሜ 13:7 |

ግጥምጥም:- ስሜና ሥራዬ አብሮ እንዲኼድልኝ፣

በቃኝ ከአምላክ ሌላ ንስሐ ገባሁኝ::

# የተበላ ዕቁብ!

ሰባኪው፣ «በዚህ ዓለም ላይ ከፍቅር ሁሉ በላይ የሆነው ፍቅር ራስን ለሌሎች አሳልፎ መስጠት ነው:: በዮሐ. 15:13 ላይ እንደተጻፈው፣ «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም»:: ይላል:: ሰው ለወዳጁ ገንዘቡን፣ ቤቱን፣ ያለውን ጥሪት ሁሉ አሟጦ ሊሰጥ ይችላል፤ ነፍሱን ግን መስጠት አይችልም:: ይህንን ማድረግ የቻለው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ስለዚህ እኛም ነፍሳችንን የምንሰጠው ለእርሱ ብቻ ሊሆን ይገባል:: እርሱ በሞቱ ሞታችንን ሽሮ፣ በቅዱስ ደሙ የገዛን ነውና ልብ በሉ:: ነፍሳችሁን ለሌላ ብትሰጡ አታገኟትም:: ለእርሱ ብትሰጡ ግን በመንግሥተ ሰማይ እንደገና ታገኟታላችሁ:: ጌታ ብቻ ነው ዋጋ ከፍሎ፣ ያውም ለመስቀል ሞት ራሱን ሰጥቶ፣ ሞቶ እኛን ከዘላለም ሞት ያዳነን» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

«በዶሮ እርባታ የሚተዳደር አንድ ገበሬ ነበር:: አንድ ቀን ባልታወቀ ምክንያት የእሳት ቃጠሎ ተነሥቶ የእርባታውን መጋዘን ከነዶሮዎቹ አቃጠለው:: ገበሬው የአካባቢውን ሕዝብ እርዳታ ጠይቆ እስከሚያስገነዝብ ድረስ ጊዜ የማይሰጠው እሳት አብዛኛውን ክፍል አወደመው:: ሕዝቡም ተሰብስቦ እሳቱ ከተባዛ በኋላ ፍርስራሹን ሲያነሣሡ የተወሰኑ ጫጩቶች ከአንድ የከሰለ ነገር ውስጥ ውልቅ ውልቅ እያሉ እየበረሩ ወጡ:: ለካስ እናታቸው በእሳት ተቃጥላ፣ እነርሱን ግን ከክንፎቿ በታች ሸሽጋቸው ኖሯል::»

አዎ፣ ይህ ለእኛ ትልቅ ምሳሌ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ እኛ ዳንን ማለት የምንችለው ግን ይህ ያደረገው ሥራ ገብቶንና ማርኮን ስናምን ነውና ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሲነገራቸው እንደተበላ ዕቁብ ችላ ይሉታል:: እርሱ ግን ሕይወት ነው:: ለዚህም ራሱ ቸሩ እግዚአብሔር ይርዳን:: አሜን!

**የቃል ጥናት ጥቅስ**:- «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3:16)::

ዮሐ. 4:14፤ 5:24

**ግጥምጥም**:- በእኔ ፈንታ ሞቶ ከሞት ያዳነኝን፣
ኢየሱስን አምኜ መንግሥቱን ወረስኩኝ::

# ዕዳ መቶ ሲሞላ አይከብድም

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን::» (ኤፌ. 1:5)

ሰባኪው:- «እግዚአብሔር ስለ ደኅንነታችን ያደረገው ነገር በዚህ ጥቅስ ላይ ግልጽ ብሎ እንደተቀመጠው ቢገባን ጌታን ቀመን ሳይሆን ተንበርክከን ብናመሰግነው ባልበዛበት ነበር:: እስቲ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ላንሣ:-

1. እኛ ከዘላለም ሞት የዳንነው በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ እንጂ በራሳችን አልነበረም:: እኛም «ዕዳ መቶ ሲሞላ አይከብድም» እንደተባለው፣ ኃጢአት በኃጢአት ላይ እየጨመርን ወደ ሞት እየገሰገስን ነበር:: ጌታ ግን እንደ በጎ ፈቃዱ ደረሰልን:: ለዚህ ነው፣ "ጌታን ተቀበልኩ ከማለት ይልቅ ጌታ ተቀበለኝ" ማለት ያለብን::
2. እኛ ከዘላለም ሞት የዳንነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ነው:: ቃሉም እንደሚል፣ ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» (ኤፌ. 2:8):: ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ ተፈጸመ ብሎ በፈጸመው የደኅንነት ሥራ ታምነን መዳን ያስፈልጋል::
3. እኛ ከዘላለም ሞት የዳንነው አስቀድሞ በተወሰነው የእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ነው:: «ዓለም ሳይፈጠር፣ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን::» (ኤፌ. 1:4):: እንደዚህ አድርጎ ያዳነን ጌታ ሁልጊዜ ልናመሰግነው ይገባል:: ለሚለው ግሩም መሠረታዊ የደኅንነት ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ አቀረቡ::

ጊዜው የስቅለት ማታ ነው:: ወንጌላዊው ከቤተሰቡ ጋር ስለበደሉና ኃጢአቱ የሞተለትን ጌታ ኢየሱስን ለማመስገን የኢየሱስን ፊልም ከፍቶ ያያል:: በፊልሙ መጀመሪያ ላይ እየተደሰቱ የቆዩት ቤተሰብ ሁሉ መጨረሻ ላይ ያለ ኃጢአቱ ሥቃይና ሞት የደረሰበትን ጌታ በመስቀል ላይ በምስማር ሲቸነከር እያዩ ፊታቸው በኀዘን ተመታ:: በተለይም የ8 ዓመቷ ልጅ ማልቀስ ጀመረች:: ፊልሙ አልቆ ከተፈጸመ በኋላ አባቷን እንዲህ ስትል ጠየቀች፣ «አባዬ ለምንድን ነው ይሄ ጥሩው ኢየሱስ የሞተው?» አባት፣ «ለእኛ ብሎ ነው የሞተው» አላት:: ቀጠለችና፣ «መቼ ነው የሞተው?» «ከዛሬ 2 ሺህ ዓመት በፊት::» በዚህ ጊዜ የ8 ዓመቷ ልጅ እየገረማት፣ «ታዲያ፣ እንዴት ለእኛ ነው የሞተው ትለኛለህ? እኔ ገና 8 ዓመቴ ነው፣ የት ያውቀኛል?» ብላው አረፈች::

አዎ፣ ዓለም ሳይፈጠር እኛም ሳንፈጠር አወቀን፣ ከአእምሮአችን በላይ በሆነው ዕቅዱም ለዘላለም አዳነን:: በእውነት የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን:: አሜን!

ግጥምጥም:- ከቶ እንደ ምን ብዬ እንዴት ላመስግንህ፣
ከሞት ስላዳንከኝ በበጎ ፈቃድህ::

| |
|---|
| ዘፍጥ. 3:15 |
| ኤፌ. 2:14-15 |

# ጊወርጊስ ወይስ ዮሐንስ?

የቃል ጥናት ጥቅስ፡- «ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።» (ዮሐ. 14፡6)

የስዕለት ልጅ ከመሆኗ የተነሣ አባትና እናቷ ሁልጊዜ የሚመለከቷት በጉጉት፥ የሚከታተሏትም በጥንቃቄና በስስት ነው። ለዚህም ነው ካደገችም በኋላ እንኳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስትገባ አድርሶ የሚመልስ ጠባቂ (body guard) የቀጠሩላት። እርሱም ሁልጊዜ የ15 ዓመቷን ልጅ እንደ መዋዕለ ሕጻናት ተማሪዎች ትምህርት ቤት አድርሶ መመለስን ተያያዘው። አንድ ቀን ግን ይህ ጠባቂ ታመመና ሥራውን አጎደለ። ቤተሰቦቿም ከጎረቤት ካሉት የዕድሜና የጾታ ተመሳሳይነት ካላቸው ተማሪዎች ጋር ትምህርት ቤት እንድትሄድ መክረው እያይዘው ሸኟት። ለካ የጎረቤት ተማሪዎች አማኞች ነበሩና ከትምህርት ቤት እንደ ወጡ ጸሎት ቤት ይዘዋት ሄዱ። እዚያም ሄዳ ወንጌልን ሰማች። ከሰማይ ሰማያት የወረደው፥ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በቀራኒዮ መስቀል ላይ የሞተውና ሞትንም አሸንፎ የተነሣው እርሱ ክርስቶስ ኢየሱስ ላመኑበት ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንደሚሰጥ፥ ነፍስንም ከገሃነመ እሳት እንደሚያድን ሰማች። በመጨረሻም ሰባኪው ጥሪ ሲያደርግ ተነሣችና አመነች (ጌታን ተቀበለች)። ደስም ብሏት ወደ ቤቷ ስትሄድ መሽቶ ደረሰች። ቤተሰቦቿም ተጨንቀው ነበርና እጅግ ተቆጥተው ጠበቋት። ስትመጣም በቁጣ፥ «የት፥ ሄደሽ ነው ያመሸሽው?» አሏት። እርሷም፥ «ቤተ ክርስቲያን» አለች። ጎሽ አሉና፥ «ለመሆኑ የትኛው ቤተ ክርስቲያን ነው የሄድሽው? ጊዮርጊስ ወይስ ዮሐንስ?» እርሷም፥ «አይ፥ አማኞች ቤተ ክርስቲያን ነው» አለች። በዚህ ጊዜ በጣም ደንግጠው፥ «ጴንጤዎች ጋ?» በማለት ጮኸው አማተቡና፥ «ለመሆኑ፥ ምን አድርገሽ መጣሽ ታዲያ?» አሏት። እርሷም፥ «ኢየሱስን ተቀብዬ መጣሁ» አለች። በዚህ ጊዜ በቁጣ ቃል ድምጻቸውን ከፍ አድርገው፥ «በይ ቀጥ ብለሽ ሂጂና ይህንን የተቀበልሺውን ኢየሱስ መልሺላቸው» አሏት። እርሷም፥ በነጋታው ለመመለስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደችና ለወንጌላዊው፥ «ትናንትና የሰጠኸኝ ኢየሱስን ቤተሰቦቼ ስላልተቀበሉት እንድታወጣና እንድትወስደው ነው የመጣሁት» አለችው። ወንጌላዊውም እንባ በዓይኖቹ እየተንቆረዘዘ የልጅቷን የዋህነት አይቶ እንዲህ አላት። «ኢየሱስን ለማስወጣት ነው የመጣሽው?» አላት። «አዎን» አለች። «እንደዚህ ከሆነ ነፍስሽ ይወጣል፥ ኢየሱስ ነፍስ ነው» አላት። እርሷም ደነገጠችና ሁሉንም ትታ ወደ ቤተሰቦቿ ተመለሰች። እነርሱም፥ «አስወጥተሽ መጣሽ ወይ?» ባሏት ጊዜ፥ «አላስወጣሁም። ምክንያቱም ወንጌላዊው ኢየሱስን ካስወጣሽ ነፍስሽም አብሮ ይወጣል» አለኝ አለቻቸው። በዚህ ጊዜ አባትና እናት የስዕለት ልጃቸውን ሞት በመፍራት እሰብ አደረጉና፥ «ነፍስሽስ ከሚወጣ እጥብቀሽ ያዢው» አሏት።

አዎ፥ ወገኖቼ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት እንጂ ሃይማኖት አይደለም። ነፍሳችንን ከገሃነም እሳት የሚያድንና ከሞት ወደ ሕይወት የሚያሸጋግር ብቸኛ አምላክ ነውና በእርሱ ታማምነን አሁኑኑ ከዘላለም ሞት እንድንድን ጌታ ይርዳን። አሜን!

ግጥምጥም:- ነፍሴን ለማዳን ነፍሱን የገደለው፥
የናዝሬቱ ኢየሱስ እርሱ ጌታዬ ነው።

የሐዋ. 4፡12
ዮሐ. 5፡24
ዕብ. 10፡39

# የፋሲካው በግ

ሕዝቡ በየዓመቱ የሚደረገውን የፋሲካ የሳምንት ኮንፍራንስ በጣም ስለሚወደውና ስለሚባረክበትም ትልቁ ቤተ ክርስቲያን የሞላው ከተቀጠረው የኮንፍራንስ ሰዓት በፊት ነው። ሰባኪውም ለዚህ ግጥም ብሎ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ለሚጠባበቀው ሕዝብ እንዲህ እያሉ መልእክታቸውን ቀጠሉ። «ዛሬ ስለ እውነተኛውና ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት የሰውን ልጅ ለማሻገር ራሱን ለመታረድ አሳልፎ ስለ ሰጠው የፋሲካው በግ (ኢየሱስ ክርስቶስ) እናገራለሁ። እርሱ ብቻውን የሰውን ልጆች ኃጢአት ተሸክሞ፥ ብቻውን ሞቶ፥ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። በእርሱ ብቻ ያመነ ይድናል። ሥጋውም ቢሞት እንኳ ነፍሱ ወደ ገነት ትገባለች። ምክንያቱም የፋሲካው በግ እርሱ ደሙን አፍስሶ ኃጢአታችንን በደሙ አንጽቶልናልና። ዛሬ የሰው ልጆች ሆይ፥ በማን ነው የታመናችሁት? ራሳቸውን ስለ እናንተ ብለው ባልሰጡና ባልሞቱላችሁ አማልእክትና ሰማዕታት ለምን ትታመናላችሁ? የነፍሳችሁ ጠበቃ ክርስቶስ ነውና በእርሱ ብቻ ታመኑ። ከፋሲካው በግ ውጭ አዳኝ የለምና ሰይጣን እንዳያታልላችሁ።» ለሚለው ስብከታቸው የሚከተለውን ምሳሌ አስረግጠው ተናገሩ።

በፋሲካ ሰሞን አንድ ሰው ከቤተሰቡ ጋር በዓሉን በደስታና በፌሽታ ለመዋል እንደተለመደው በግ ለመግዛት ወደ ገበያ ሄዱ። መርጠው አማርጠው በዓይናቸው የሞላውን በሚችሉት ዋጋ ገዙና በረጅም ገመድ የበጉን አንገት አስረው እየሳቡ በደስታ ወደ ቤታቸው መሄድ ጀመሩ። በመንገድም ሆነው፥ «አሁን ቤቴ ሄጄ ይህንን በግ አርድና ከቤተሰቤ ጋር ስፈልግ ጥብስ፥ ስፈልግ ዱለት፥ ስፈልግ ቀይ ወጥ እያማረጥኩኝ በመብላት ስደሰት እውላለሁ» እያሉ ይመኛሉ። በየመንገዱ የሚያልፈው ሰው ሁሉ ግን ሰውዬውን እያዩ ይስቃሉ፥ ግማሹም ይገረማል። ግማሹም፥ «ሰውዬው ምን ነካው? ይላል። ለካስ እንደዚያ ለብዙ ነገር የተመኙት ከቤተሰቤ ጋር ስደሰትበት እውላለሁ ያሉት የፋሲካው በግ ከገመዱ ሾልኮ አምልጧል። ለካ ሰውዬው ባዶ ገመድ ነበር የሚጎትቱት– ባዶ ገመድና ባዶ ምኞት።

እኛስ አንባቢ ሆይ፥ የታመነውንና እውነተኛውን የፋሲካ በግ ክርስቶስን ይዘናል ወይስ እንደ ሰውዬው ባዶ እምነት ይዞን ይዘን የምንገሰግሰው? ከሰማይ ሰማያት የወረደውን፥ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ላይ ስለ ሁላችን ኃጢአት የሞተውንና የተነሣውን የፋሲካውን በግ ታምነን ለመንግሥቱ እንድንበቃ መንፈስ ቅዱስ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም:- ከሞት የሚያድንህ ክርስቶስ ብቻ ነው፥
ከእርሱ ሌላ ሁሉም የከንቱ ከንቱ ነው።

> ዮሐ. 4:25–26
> ቲቶ 2:11–13

# ይሉኝታ ይገድላል

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ኑኃሚን ከአርስዋም ጋር... ምራትዋ ሩት ተመለሱ::» (ሩት 1:22)

ሰባኪው፣ «ዛሬ የምሰብከው በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስ ነው:: ወገኖች፣ እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው:: በቃሉም፣ «ብትመለሱ እመልሳችኋለሁ::» ብሏልና ዛሬ ያለን ክርስቲያኖች በተለያየ ኃጢአት ውስጥ የወደቅን ብንኖር እንመለስ:: ሕዝቡ ሁሉ የሚያውቀው ኃጢአት የሠራን በሕዝቡ ፊት ንስሐ ገብተን እንመለስ:: እግዚአብሔርና እኛ ብቻ የምናውቀው ኃጢአት የሠራን በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ገብተን እንመለስ:: ይሉኝታና ፍርሃት ሸብቦን ንስሐ ሳንገባ ከነኃጢአታችን ወደ ሲዖል አንውረድ:: ከቃሉ እንደምናየው ኑኃሚን ባዶዋን ተመለሰች ጌታ ግን ባዶነቷን ሞላ:: በምሬት ነው የተመለሰችው፣ ጌታ ግን ምሬቷን ወደ ደስታ ለወጠ:: በመመለስ ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለም:: ከኑኃሚን መመለስ ውስጥ ሩት ተገኘች:: በመመለስ እራሳችንንና ሌሎችንም እናድናለንና ዛሬውኑ እንመለስ:: ንስሐ ገብቶ በመመለስ የሚገኘውን ትርፍ ደስታ፣ እረፍትና ሕይወት ሰይጣን ስለሚያውቀው እንዲህ እያለ ያጨልምብናል፣ <ጓደኞችህ ምን ይሉሃል? ሕዝቡ ሁሉ ያጠቋቁምብሃል፣ እግዚአብሔርም አይቀበልህም::> ነገር ግን እግዚአብሔር መሐሪ፣ ሕዝቡም ተቀባይ ነውና ተመለሱ:: አለበለዚያ ከነኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ::» ለሚለው አስደናቂና ግሩም ለሆነ ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

ሁለቱም በአንድ የመዘምራን ቡድን ውስጥ የሚያገለግሉ ወጣቶች ነበሩ:: በአገልግሎታቸው ብቻ ሳይሆን በሥራቸውም በአንድ ላይ ሆነው በንግድ ሥራ ነበር የሚተዳደሩት:: ጊዜ እየረዘመ ሲሄድ ቤተ ክርስቲያን መሄዱንም ሆነ ማገልገሉን እየቀነሱ መጥተው መጨረሻ ላይ ከነአካቴው ሁሉንም ትተው ንግዳቸውን ብቻ ቀጠሉ:: ያለ እግዚአብሔር በራስ ጥረት መሳካት አይገጥምምና ንግዱንም ከሠሩ:: ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ብዙ ጣሩ፣ ግን አልሆነም:: በመጨረሻም አንደኛው የእግዚአብሔር መንፈስ ወቅሶት መመለስ እንዳለበት ወስኖ ለጓደኛው ቢነግረው እምቢ አለ:: «የድሮ የመዘምራን ቡድን ጓደኞቻችን ምን ይሉናል? የሕዝቡ ዓይን ይበላናል:: ይህንን ሁሉ አድርገን እግዚአብሔር የሚቀበለን አይመስለኝም::» ጓደኛው ግን ይህን ሁሉ ሳይሰማ ወደ አምላኩ ተመልሶ ንስሐ ገባና ከነፍሱ አዳኝ ጋር ታረቀ::

በዚህ ሁኔታ ደስ ብሎት እየተመላለሰ እያለ አንድ ቀን እንደዚሁ የንግድ ዕቃ ለማምጣት ከጓደኛው ጋር ወደ ክፍለ ሀገር ሲሄድ የመኪና አደጋ ይደርስና ሁለቱም ሳይመለሱ እስከወዲያኛው አንቀላፉ::

አዎ፣ ወገኖቼ፣ ከዚህ ታሪካዊ ምሳሌ የምንረዳው የመዳን ቀንና ንስሐ የምግባት ቀን ዛሬ ነው፣ ነገ ምን እንደምንሆን አናውቅም:: ንስሐ አድራሻን ይቀይራል:: አንዱ ወጣት ንስሐ ገብቶ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሲሄድ፣ ሌላው ደግሞ ይሉኝታን ፈርቶ ንስሐ ሳይገባ ወደ ገሃነም እሳት ሄዷል:: ይሉኝታ ይጎድላልና ዛሬውኑ ንስሐ እንድንገባ ጌታ ይደግፈን::

**ግጥምጥም፡- ንስሐ ገብቼ ልታረቅ ከአምላኬ፣**
**ምሥጢሩ ገብቶኛል እንዲህ መታወኬ::**

ምሳ. 28:13
ኢሳ. 1:18-20

## *ክፍል 10*

## *ለእግዚአብሔር ስለ መሰጠትና መስጠት*

# ኮርሽምሽምሽምሽም

**የቃል ጥናት ጥቅስ፣ «...በዚህ ቸር *ሥራ* ደግሞ ትረፉ።» (2ኛ ቆሮ. 8:7)።**

ሰባኪው፡ አጽንኦት ሰጥተው የሚናገሩት ስለ መሰጠት ነበር። «ዛሬ ለመስጠት አቅም ያጣነው መጀመሪያ ቀድመን ራሳችንን፣ ትዳራችንን፣ ሥራችንንና በአጠቃላይ ሕይወታችንን ስላልሰጠን ነው። የተሰጠ ሰው ለመስጠት ጉልበት ይኖረዋል። የምንሰጠው ደግሞ ሲተርፈን ብቻ። ከጉድለታችንም ነው። ልክ፣ «የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስነታቸውን ባለጠግነት አብዝቶአል።» (2ኛ ቆሮ. 8:2) እንደተባለው የእግዚአብሔር ቃል ልናደርግ ይገባል ፕሮግራም ውስጥ የገባን ነገር ወይም አንድ ነገር ሊፈጸምበት የታቀደን ገንዘብ መስጠት ከባድ ቢመስልም ግን እግዚአብሔር የበለጠ አዘጋጅቷልና ፕሮግራሙን እንኳ ትተን ለእርሱ ልንሰጠው ይገባል።» እያሉ ለተሰበሰበው ሕዝብ መናገራቸውን ይህንን ምሳሌ አስከትለው ቀጠሉ።

አንድ ቀን ከቤተሰብ ጋር ቤት አብረን ጊዜ እያሳለፍን ሳለ የመጨረሻዋ ልጅ አንድ ሥራ ሠርታ፣ «ምን ላርግልሽ?» ስላት፣ ከረሜላ ገዝተህ ካልሸለምከኝ ስላለች ሁለት ደስታ ከረሜላ ገዛሁላትና መብላት ጀመረች። አንደኛውን ጨርሳ ሁለተኛውን አፍዋ ውስጥ እንዳስገባች የልጄ አፍ ውስጥ የገባውን ከረሜላ መብላት ደስ ስላለኝ እንድትሰጠኝ ጠየቅኳት፣ እርሷም ግንባሯን እያኮሳተረች እንደማትሰጠኝ መለሰችልኝ። እኔም እንድትሰጠኝ፣ «እኔ አይደለሁ እንዴ የሰጠሁሽ? እባክሽ ስጭኝ» ብዬ መለመኔን ቀጠልኩ። በዚህ መሃል አንድ ድምጽ ከአፏ ውስጥ ሰማሁ። ለካ ከረሜላውን ኩርሽምሽምሽምሽም አድርጋ እንደማትሰጠኝ የመጨረሻውን መርዶ እያሰማችኝ ነበር።»

አዎ፣ ፕሮግራም ውስጥ የገባውን ነገር ለአባቷ ለመስጠት ይህች ልጅ የተቸገረችው ስስት እና ራስን አለመስጠት ስላጠቃትና የነገሩም ጣፋጭነት ስለአጓጓት ነው። እኛስ እንደዚህች ሕፃን ነን ወይስ አባቴ የበለጠ የጣፈጠ ነገር ይሰጠኛል ብለን በመጨከን የምንሰጥ ነን? ስስታችንን እና ስሜታችንን ገትተን ፕሮግራም ውስጥ ያስገባነውንም ነገር እንኳ ለጠየቀን አምላካችን በደስታ እንድንሰጥ እግዚአብሔር ይርዳን።

**ግጥምጥም፡-** ለቸሩ እግዚአብሔር *ሥራ* ሠርቼ፣
እኖራለሁ እንጂ ሳልኖር ተከፍቼ።

**2ኛ ቆሮ. 8:8-11**
**ፊልጵ. 4:19**

# ኢንቨስተሩ!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለዘሪ ዘርን ለመብላትም እንጀራን በብዙ የሚሰጥ እርሱም የምትዘሩትን ዘር ይሰጣችኋል ያበረክትላችሁማል፣ የጽድቃችሁንም ፍሬ ያሳድጋል» (2ኛ ቆሮ. 9:10)

«ሁሉ ከእርሱ ነው:: ከእኛ የሆነ ምን አለ? ወደዚህስ ዓለም ስንመጣ ምን ይዘን መጥተናልና» በዕለቱ የሰባኪው ዋና የመልእክታቸው ክፍል ነበር:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ባዘጋጀችው ዓመታዊ የገንዘብ ማሰባሰቢያ /Fundraising/ ፕሮግራም ላይ ሰባኪው ቀጠሉ:: «ሁሉን የሰጠን እግዚአብሔር ነው:: ሁሉንም መልሰን ለእርሱ ልንሰጠው ይገባል:: ለጌታ ሰጥቶ የከሰረ የለምና የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር፣ የቄሳርን ለቄሳር ስጡ:: የእግዚአብሔርን ገንዘብ አትስረቁ፤ አስራቱን፣ መባውን፣ በኩራቱን ወደ ጎተራው አስገቡ:: አምላኬ እንዲሰጠን፣ እንዲባርከን ጸልየን ከሰጠን በኋላ ለእርሱ ለመስጠት አንሰስት:: ጋብቻችን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው:: በዚህ ምድር ላይ ሀብታም የለም፣ ባለአደራ እንጂ! ሀብቱማ የእግዚአብሔር ነው:: እኛ ሰዎች የባለሀብቱ ሀብት ጠባቂና አንቀሳቃሽ ባለአደራዎች ነን:: ባለሀብቱም (ኢንቨስተሩ) እግዚአብሔር አባታችን ነውና ለአባታችን የአባታችንን ሀብት ለመስጠት መሳሳት የአደራነትን አገልግሎት አለመወጣት ነው::» ሰባኪው ይህንን ትምህርታቸውን ለማጠናከር ቀጣዩን ምሳሌ አስከትለው ተናገሩ::

«አንዲት ልጅ ትምህርቷን ከጨረሰች በኋላ ሥራ ፈትታ ለብዙ ዓመታት ቁጭ አለች:: ወጣ ብላ ሥራ ለመፈለግ በጣም ፈሪና ዐይናፋር ከመሆኗ የተነሣ፣ ይህንን ችግሯን የተረዱ ቤተሰቦቿ የወደፊት ሕይወቷ ስለአሳሰባቸው አባቷ ከአንድ የግል ድርጅት ጋር ተነጋገሩና ሥራ አስገቧት:: ይኸውም በየወሩ ደመወዟን እርሳቸው ሊከፍሉ፣ ድርጅቱ ሠራተኛ እንደሚፈልግ ገልጾ በማስታወቂያ በማወዳደር እንዲቀጥራትና በየወሩም የአባቷን ገንዘብ እየተቀበለ እንዲከፍላት እርሷ ሳታውቅ በምሥጢር ይህንን ተነጋገሩ:: እናም አባቷ የሥራ ማስታወቂያ እንደወጣና እዚያም ድርጅት ሄዳ እንድትወዳደር ጠቆሟትና ሄዳ ማመልከቻዋን አስገባች:: እንዳለፈችም ይነገራትና ሥራዋን ትጀምራለች:: ሥራ በማግኘትዋም ከቤተሰቧ ጋር ደስታዋን ትገልጻለች:: የሁለት ወራት ደመወዟን ከበላችም በኋላ አባቷ

በሦስተኛው ወር፣ "እስከ አሁን አየሁሽ፣ ምንም የደስ ደስ አልጋበዝሽኝም፣ እስቲ በዚህኛው ወር ደመወዝሽ ወጣ እንብልና ጋብዥኝ ሲሏት፣ እንዲህ ብላ መለሰች:: "አይ አባዬ፣ ለጸጉሬ ቅባት፣ ለልብሴና ለሌሎችም ጌጣጌጦች አይበቃኝምና ልጋብዝህ አልችልም:: ይቅርታ!" ብላቸው አረፈች:: በገዛ ገንዘባቸው::»

አዎ፣ ወገኖቼ እግዚአብሔር እንዲሁ ነው:: ይሰጠንና፣ "እስቲ ከአሥሩ አንዱን እጅ ለእኔ ስጠኝ ሲለን፣ አይ፣ ለዚህ ለዚያ ለማይበቃኝ አልሰጥህም ብለን በገዛ ገንዘቡ እንከለክለዋለን:: ምንኛ ምስኪኖች ነን:: እስቲ ተመልከቱ የዚህች ልጅ አባት ለምትሠራበት ድርጅት ገንዘብ መስጠት ቢያቆሙ ምን ይውጣት ይሆን? እኛም እንደዚሁ ነን:: ወገኖቼ፣ ለዘሪ ዘርን የሚሰጠው እግዚአብሔር እንደዘራ እንዲሰጥ ነውና ለእርሱ ካለን ሁሉ በላይ በደስታ እንድንሰጠው ጌታ ይርዳን:: አሜን::

2ኛ ቆሮ. 9:6፣7
ሮሜ 11:36
ሚልክ. 3:7-12

ግጥምጥም:- የእኛ ለእኛ እኮ ነው ብለን የምንለው፣
ምን ኖሮን ነው ከቶ ይዘን የመጣነው::

# የፈረንጅ ላም

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፣ የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።» (ሉቃስ 6:38)

መጋቢው፣ «የክርስቲያኖች ኑሮ የማያድገው ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ ስለማንሰጥ ነው የሚል ነው። ዛሬ ኑሮአችን የተትረፈረፈ መሆን ሲገባው፣ የቤተሰባችንና የአገራችን ኑሮ ከእጅ ወደአፍ ሆኖ ያለው ለምንድን ነው? ብንል ስለማንሰጥ ነው። ወገኖች፣ ለእግዚአብሔር የተሰሰተ ኃብት በረከት የለውምና እንስጥ፣ ለድሆች እናካፍል። ለድሃ የሚያካፍል አይደኸይም፣ ለድሃ የሚሰጥ ለእግዚአብሔር እንዳበደረ ነው የሚቆጠረውና ራሳችን ለራሳችን ብቻ እናከማች። ከእግዚአብሔር ጋር እናከማች። ብልጥ ልጅ በአባቱ ኪስ ያጠራቅማል እንደሚባለው፣ በአባታችን በእግዚአብሔር ጎተራ እናጠራቅም። ያን ጊዜ በረከት ይኖራል።» ለሚለው ትምህርታቸው መጋቢው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ልጅ የፈረንጅ ላም በ5 ሺህ ብር ለመግዛት አስቦ 50 ሳንቲም በአባቱ ኪስ ማስቀመጥ ጀመረ። የሚያገኘውን ሳንቲም ሁሉ እያስቀመጠ በስድስት ወር ውስጥ አምስት ብር ደረሰ። ታዲያ በዚህ ሁሉ በነጋ በጠባው ልጁ አባቱን፣ «የፈረንጅ ላም ለመግዛት ብሬ አልሞላም ወይ?» እያለ ይጨቀጭቃል። ዓመት ሲሆነው ብሩ እንኳን 5 ሺህ ብር ሊሞላ አሥርም ብር አልሞላም። ይህ ትንሽ ልጅ ግን የፈረንጅ ላም የመግዛት ጉጉቱ ስለጨመረ በነጋ በጠባው አባቱን፣ «አልሞላም ወይ?» እያለ መነዝዙን ቀጠለ። በዚህ ጊዜ አባቱ የልጁ ንዝነዛ ስለበዛበት፣ ከዚህ ሁሉ እኔ ብገዛለት ይሻላል ብሎ 5 ሺህ ብሩን አውጥቶ ገዛለት።

አዎ፣ የእኛ አይሞላምና ከእግዚአብሔር ጋር እናጠራቅም። ያን ጊዜ እግዚአብሔር የልባችንን መሻት ይሞላል። የተትረፈረፈውንና የተጨቆነውን መስፈሪያ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም እናየዋለን። ቤታችንም አገራችንም ተባርካ ለሌላውም ዓለም የምንተርፍ ሰዎች እንሆናለን።

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለድሃ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል።» (ምሳሌ 19:17)

ግጥምጥም:- አንዱ ምክንያት ለካ ለዚህ ድህነቴ፣
አለመስጠት ኖሯል ወይኔ ስስቴ።

(2ኛ ቆሮ. 8:1-2)

# ዲቪ ቢወጣልኝ!

**የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እርስዋም ለባሪያህ ወንድ ልጅ ብትሰጠኝ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ:: ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም ብላ ስዕለት ተሳለች::»**

ቄሱ በቤተ ክርስቲያናቸው ስንበትን ምክንያት አድርገው ለተሰበሰቡት ምእመናን ሁሉ የዕለቱን መልእክታቸውን ለማቅረብ ዝግጅታቸውን አጠናቅቀው የፊት ወንበር ይዘዋል:: የዕለቱም ፕሮግራም መሪ የያዛቸውን ከመልእክት በፊት ያሉትን የዕለቱን ፕሮግራሞች ካጠናቀቀ በኋላ ቄሱን ጋበዛቸው፣ እርሳቸውም መልእክታቸውን ቀጠሉ:: «በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ከጊዜው ጋር በብዙ ሁኔታቸው እየተለዋወጥን ጌታን እያሳዘንን ያለን ይመስለኛል:: ይህንን ልል የቻልኩበት አንዱ ምክንያት ለምሳሌ፣ በአፋችን ለእግዚአብሔር የተናገርነውን ስዕለት በተግባር ስንፈጽም ብዙ አይታይም:: ወገኖች፣ ባንሳል ይሻለናል:: ስንቶች እንሆን፣ "ሥራ ብትሰጠኝ የመጀመሪያ ደመወዜን ላንተ እሰጣለሁ::" ብለን ሥራ አግኝተን ያልነውን ለመፈጸም የተቸገርን:: ስንቶች እንሆን፣ "ማኅጸኔን ብትከፍትልኝ የምወልደውን ልጅ ለአንተ አገልጋይ እንዲሆን እሰጣለሁ::" ብለን እንደ ሐና ነገር ግን ልጆቻችንን እንደሚገባ ካለማሳደጋችን የተነሣ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆናቸው ቀርቶ የሰይጣን አገልጋዮች የሆኑብን:: ስንቶች እንሆን፣ "ዲቪ ቢወጣልኝ / ወይም በተለያየ ዕድል /ከአገር ውጭ ብወጣና በዚያም የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቼ ብኖር በኢትዮጵያ አገሬ አንድ ቤተ ክርስቲያን እተክላለሁ የተወሰኑ አገልጋዮችንም ቀለብ እችላለሁ::" ብለን ከተጸለየልንና ሁሉም ተሳክቶ ከተመቻቸን በኋላ እንደዚህ ብለን ስዕለት መሳላችንን ጭራሽ የምንረሳና ትዝ የማይለን:: ቅዱሳን እግዚአብሔር ከልጆቹ አፍ የወጣውን ስዕለት ይፈልገዋልና ፈጽሞ እግዚአብሔርን ማታለል አይቻልም::» ለሚለው መልእክታቸው ይህንን ቀጣይ ምሳሌ ተጠቀሙ::

አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ስዕለት ተሳለ፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ከዚህ በኋላ ከማገኘው ሁሉ ግማሹን ለአንተ እሰጣለሁ:: 100 ብር ብትሰጠኝ ግማሹ ያንተ ነው፣ አምስት መቶ ባገኝ ግማሹ ያንተ ነው፤ 1 ሺህ ባገኝ ግማሹ ያንተ ነው::» መቼም እግዚአብሔር ቸር ነውና ይህን ስዕለት ተስሎ ጨርሶ በመንገድ ላይ ሲሄድ ጭር ያለ አካባቢ 50 ብር ያገኛል፤ በዚህ ጊዜ የተሳለው ትዝ አለውና እንዲህ አለ፣ «እግዚአብሔር እንደማልሰጥህ አውቀህ የራስህን ድርሻ ወስደህ የእኔን ስለላክልኝ አመሰግንሃለሁ::»

አዎ፣ የብዙዎቻችን ስዕለት ውጤቱ ከዚህ ሰውዬ ብዙ የተሻለ አይመስልምና ለጌታ የገባነውን ቃል ኪዳን /ስዕለት/ እንፈጽም:: አንዳንዶች፣ «ስዕለት የብሉይ ኪዳን ነው እንጂ የአዲስ ኪዳን አይደለም:: ክርስቲያን አይሳልም» ይላሉ:: ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት አይደለምና እንመለስ:: የተሳልነውንም እንድንፈጽም ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ከአፌ የወጣውን የከንፈሬን ፍሬ::
ስዕለቴን ልፈጽም ሳያልፍ ዘመኔ::

**መሳ. 11:29-40**
**ዘፍጥ. 20:20-22**
**መክ. 5:4-5**

# ኑሮ ጨምሯል

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እናንተ፣ ይህ ሕዝብ ሁሉ፣ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ።» (ሚልክ. 3:9)

ሰባኪው፣ ለእግዚአብሔር ላለመስጠት ብዙ ምክንያቶችንና ዘዴዎችን መጥቀስ የለብንም። የእግዚአብሔር ቃል የሚለው ስጡ ነው። ለእኔ ሰጥታችሁ ፈትኑኝ ነው ያለው። እኛ ሳንሰጥ እግዚአብሔርን፣ "ለምን በረከት አጣሁ? ሲሳይ ከድንኳኔ ጠፋ?» ብለን መፈታተንና ማማረር የለብንም። ሰይጣንና የአሁኑ ዘመን ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ አይፈቅዱም። የሰይጣንንም ምክንያት ማስተናገድ የለብንም። ሰይጣን ኑሮ ጨምሯልና ዛሬ ተወው ነገ ትሰጣለህ እያለ ያታልለናል። ሁሉም ነገር ቢጨምር የሚያኖረን የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ጨመረ መርሳት የለብንም። ቃሉ እንደሚል፣ «መኖሪያህ እግዚአብሔር ነው፤ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው።» ይህንን መታመን አለብን። ለእግዚአብሔር ላለመስጠት ድህነት እንኳ ምክንያት አይሆንም። ያቺ ድሃ መበለት ሁለት ዲናር ሰጥታ ከሃብታሞቹ በላይ አብልጣ ሰጠች ተብሎላታልና። ሦስት ነገሮችን እግዚአብሔር በደስታ እንድንሰጠው ይጠብቅብናል:- ራሳችንን፣ ያለንን እና ጊዜያችንን። ለእግዚአብሔር ላለመስጠት ምንም ዓይነት ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም።» ለሚለው ጠንካራ አሳዳጊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«ሦስት አማኞች አንድ ቀን ለእግዚአብሔር ገንዘባቸውን እንዴት እንደሚሰጡ ቁጭ ብለው መነጋገር ጀመሩ። አንደኛው ተነሣና፣ "እኔ ገንዘቤን ለእግዚአብሔር የምሰጠው ደመወዜን እንደተቀበልኩ አንድ ቦታ እቆምና በዙሪያዬ ሰፊ ክብ መሥመር አከባለሁ። ገንዘቤን ወደ ላይ እወረውራለሁ። ከክቡ ውስጥ የወደቀው የእኔ ነው፤ ከክቡ ውጭ የወደቀው የእግዚአብሔር ነው" አለ። ሁለተኛው አማኝ ተነሣና፣ "እኔ ግን ውጭ የወደቀው ለእኔ ነው፣ ውስጥ የገባው የእግዚአብሔር ነው አለ። ሦስተኛው አማኝ ደግሞ እንዲህ አለ፣ "የእኔ ከእናንተ ትንሽ ይለያል። በዙሪያዬ የክብ መሥመር አላከብም። ነገር ግን ያለኝን ገንዘብ በሙሉ ወደ ላይ እወረውራለሁ። የእኔ የሆነው ወደ እኔ ይመለሳል፤ እግዚአብሔር ደግሞ የራሱን በዚያው ወስዶ ያስቀራል" አለ።

እነዚህ ሰዎች ጤንነት፣ ሰላምና ችሎታ ችሮ ገንዘብ ለሰጣቸው አምላክ ለመስጠት ሁሉም ፈቃደኞች አይደሉም። እንዲያውም ልብንና ኩላሊትን የሚያውቀውንና የሚመረምረውን ጌታ ሲያታልሉት ይታያሉ። እኛስ? ለእግዚአብሔር መስጠት ትርፍ እንጂ ኪሣራ የለውም፣ ማግኘት እንጂ ማጣት የለውም። ይህንን ተረድተን ያለ ምንም ሰበካ በደስታ እንድንሰጠው ጌታ ይርዳን። አሜን።

| | |
|---|---|
| ግጥምጥም:- መቀበል በመስጠት መሆኑን አውቃለሁ፣<br>ለሚሰጠኝ ጌታ መልሼ እሰጣለሁ። | ማር. 12:42<br>ሉቃ. 6:38 |

# እንደ አንበጣዎች ነን

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን...» (ዘኁል. 13:33)

ሰባኪው:- «እኛ ክርስቲያኖች በእውነትና በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት በመታመን በንጹሕ ሕሊና መሄድ እንጂ ላይሆን በሚችል ሥጋ በፈጠረው ስሜታዊ ግምት መሄድ የለብንም:: በእግዚአብሔር እውነት ላይ እንጂ በሥጋዊነት ግምታዊ አስተሳሰብ ላይ መታመስ የለብንም:: ለምሳሌ፣ ሁለት ሰዎች በግቢው ውስጥ ወይም በመንገድ ዳር ቆመው እያወሩ በሩቅ ብናይ ሥጋችን የሚለን፣ "ስለ አንተ ነው የሚያወሩት፣ እያሙህ ወይም እያሴሩብህ ነው::" ይህ የተዛባ ግምት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ስለ አንድ ነገር በጉባኤ ላይ ማስታወቂያ ስትናገር፣ "እኔን ለመንካት ወይም ከአገልግሎትና ከቤተ ክርስቲያን ለማባረር ነው" ማለት የለብንም:: በእርግጥ የሠራነው ኃጢአት ካለና መንፈስ ቅዱስ ከወቀሰን ንስሐ እንግባ:: አለበለዚያ በአገር ሰላም ራሳችንን አናስጨንቅ:: እስራኤላውያን፣ "በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን" አሉ:: የተሳሳተ ግምት የተሳሳተ አመለካከትን ይወልዳል:: እነርሱ በእግዚአብሔር ክብር የተፈጠሩ ሰዎች ናቸው እንጂ አንበጣዎች አይደሉም:: ስለዚህም ተጉዱ፣ በአፋቸው በምድረ በዳ እንሞታለን እንዳሉት እንደ አንበጣ በየበረሃው ሞተው ቀሩ:: የተሳሳተ ግምት ይጎዳል::» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

በማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አዲስ የተጠመቁ 40 አማኞች የጌታን እራት እንዲወስዱ የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት እያስፈጸምኩ ነው:: ሁሉም አማኞች በአንድ እጃቸው ደሙን የሚወክለውን ወይኑን ይዘዋል:: በሌላ እጃቸው ደግሞ ሥጋውን የሚወክለውን ኅብስቱን ይዘዋል:: እኔም ሳይገባቸው እንዳይወስዱ የሚናዘዙት ኃጢአት ካለም እንዲናዘዙ በጸሎት ሆነን እያስተማርኩ ነው:: በዓይኔ ቀና ብዬ ሁሉንም ስመለከት አስገራሚ ነገር አየሁ:: እንደዚያ ቀን አደብ ገዝታ የማታውቀው የአምስት ዓመቷ ትንሺ ልጄ ከተጠማቂዎቹ በስተመጨረሻ ላይ እጆቿን አጣምራ በሥነ ሥርዓት ቁጭ ብላ አየኋት:: በመጨረሻም፣ ሁሉም የጌታን እራት የሚወስዱበት ጊዜው ደረሰና በአንድ ላይ እንዲወስዱ አዘዝኩኝ፣ ሁሉም ወሰዱ:: አመስግነን ከጨረስኩ በኋላ ያቺ በሥነ ሥርዓት ተቀምጣ የነበረችው ልጄ

ከመቀመጫዋ ተነሥታ ፊቷን አኵሳትራ ወደ እኔ መጣችና፣ «አባዬ፣ ኩኪሱ እኔ ጋ ሳይደርስ ለምን አለቀ?» ብላ አለቀሰች።

አዎ፣ ወገኖቼ፣ ይህች ልጅ የጌታን ራት እንደ ሠርግ ኩኪስ በመቁጠር በተሳሳተ ግምት ተጐዳች። በከንቱ እምባዋን አፈሰሰች። እርሷ የገመተችው፣ "አባቴ የብስኩቱ አዳይ ነው፣ እኔም የእርሱ ልጅ ነኝ፣ እንደ ፈለግሁ እጠግባለሁ" ብላ ነበር። ነገር ግን አልሆነም። በእኛም ሕይወት እንዲሁ ነው። አባቴ እግዚአብሔር ነው፤ እኔም ልጁ ነኝ ብለን ያልሆነ ግምት ገምተን ነገር ግን ሳይሆን ቀርቶ የተጐዳን እንኖር ይሆን? እግዚአብሔር ከገመትነውና ከምናስበው በላይ ማድረግ የሚችል ነውና ትክክል ካልሆነ ሥጋዊ ግምታችን ወጥተን እምነታችን በእርሱ የእውነት ተስፋና ቃሉ ላይ ብቻ እንዲመሠረት ጌታ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም፡- ያልሆነውን ግምት በሥጋ እየገመትኩ፣
ጌታ በሌለበት በምድረ በዳ አለቅኩ።

| |
|---|
| ዘኁል. 14:36-38 |
| ፊልጵ. 2:3 |

## ችግሬ ክሶኝ ተከሰከሰ!

የቃል ጥናት ጥቅስ- «ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።» (ዮሐ. 14:14)

ሰባኪው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲህ እያሉ ያስተምራሉ። «ወገኖቼ፣ እምነት የሌለው ሰው ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርንም እራሱንም ደስ ማሰኘትና ከሚመጣው ቁጣ ማምለጥ አይችልም። የክርስትና ሕይወት የተመሠረተው በእምነት ላይ ነው። ምንም ከባድና አስቸጋሪ ነገር በሕይወታችን ይግጠመን በእግዚአብሔር ታምነን ለእርሱ ካስረከብነው እንደ ቃሉ ይፈታዋል፣ ያስተካክለዋል። ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለም። የእኛን እምነት የሚፈታተኑ ጉዳዮች እንኳን ቢኖሩ ለእግዚአብሔር ምኑም አይደሉምና ለእርሱ እናሳይ። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ያለጥርጣሬ በእርሱ ሁሉን ቻይነት የሚታመን ልብ ነው።» ለዚህም ግሩም የሆነ ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

«አንድ መጋቢ በስብከት ተራው ቆሞ ስለ እምነት እንዲህ እያለ ይሰብካል። "የሰናፍንጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ተነቅለህ ወደ ባሕር ሂድ ብትሉት ይሆናል።" በዚህ ጊዜ በጉባኤው መካከል ቁጭ ብለው ይሰሙ የነበሩ አንዲት አሮጊት፣ "ይህ ማለት ካመንኩ በእኔ የሰናፍንጭ መሬት ላይ ያለው ትልቅ ቋጥኝ/ተራራ ድንጋይ/ ይናዳል ማለት ነው" ብለው አመኑ። ስብከቱም እንዳበቃ ወደ ኋላ ቀሩና መጋቢውን አግኝተው፣ "ዛሬ እግዚአብሔር የተናገረው እኔን ነው። ስለ እምነት ቅድም ስትሰብክ ትልቁ ተራራ ይናዳል ብለሃል። እኔም አምናለሁ። አንተም ጸልይልኝ። በተለይ የሰናፍጭ መሬቴ ላይ ያለው ተራራ እንዲናድ" ቢሉት። "አይ፣ እኔ ግን የሰበኩት እርሱን ሳይሆን፣ በሕይወታችን ላይ ያሉ የተለያዩ ተራራዎችን ነው" ብሎ መንፈሳዊ ቢያደርግባቸውም፣ "እኔ አምናለሁ፣ የእኔን የሰናፍጭ መሬት ተራራ ነው ጌታ ያለው" አሉት። መጋቢውም፣ "እንደ እምነትዎ ያድርግልዎት" ብሎ ሸኛቸው። እርሳቸውም በእምነት ጸሎታቸውን ቀጠሉ። ጌታም ጸሎታቸውን ሰማ። የአውራ ጉዳና መንገድ ሥራ ትልቅ መንገድ ለአገሪቱ ሲሠራ መንገዱ የሚያልፈው በሴትየዋ የሰናፍጭ መሬት አካባቢ በመሆኑ፣ ባለሙያዎቹ ያ ትልቅ ቋጥኝ ድንጋይ ተከስክሶ ለመንገድ ሥራቸው

እንደሚሆን አሰቡና ሴትዮዋን ጠይቀው ገዝተው በዶዘር በማንሣት የሰናፍጭ መሬቱን የተስተካከለ ሜዳ አደረጉት:: በዚህ ጊዜ ሴትየዋ እግዚአብሔር የየዋህነት የእምነት ጸሎታቸውን እንደ መለሰ ስላዩ እንዲህ አሉ፣ "እስከ ዛሬ ብዙ ሰናፍጭ እንዳለ መሬት የተዋጋኝ ችግሬ ከሶኝ ተከሰከሰ፤ አሜን::"»

በእርግጥ ለሚታመኑበት አምላክ እንዲህ ያደርጋል:: ዛሬም ያለ ጥርጣሬና ማመንታት ነገራችንን ሁሉ ለጌታ ብንሰጠው ያስቸገረንን ችግር አስቸግሮ መልሶ እኛን እንዲጠቅመን ወይም ለዘላለም ከነመታሰቢያው እንዲወገድ ያደርገዋል:: እምነት ውኃን ይከፍላል፣ በውኃ ላይ ያስኬዳል:: ጥርጣሬ ግን ያሰምጣል:: በጥርጣሬ ተሞልተን በዚህ ዓለም ሰምጠን እንዳንቀር እግዚአብሔር እምነትን ያብዛልን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ተራራን የሚንድ ሰጥቶህ ጌታ እምነት፣
የትኛው ተራራ ሊቆም በአንተ ፊት::

| |
|---|
| ዘፍጥ. 18:14 |
| ዘካር. 4:7 |

# እናቴ ጆሮዬን በላችው

ሰባኪው፣ «ዛሬ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ በራሳችን ድካም፣ ጥረትና ጥበብ ነገሮችን ለማሳካት ወይ የምንፈልገውን ለማግኘት እንደማንችል ከሕይወቴ ምሳሌ ጋር እያዛመድኩ እነግራችኋለሁ:: የእግዚአብሔር የአምላካችን ቃል እንደሚል፣ "ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የበላ ተድላንስ የቀመሰ ማን ነው?" ይላልና:: ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ነገር ሊሆን አይችልም፣ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ምንም ሊያግደው አይችልም:: አንዳንድ ጊዜ የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት እንድንችል በራሳችን ጥረት እንድንሄድ ሰይጣን ያታልለናል:: ግን የጌታ እጅ ከሌለበት አይሆንም:: ከሆነም በጌታ ቸርነትና ፈቃድ እንጂ የተጠቀምነው ጎዳና ሰምሮ ወይም የግል ጥረታችን ታክሎበት አይደለም::»

«ትዝ ይለኛል አባቴ የነገረኝ፣ እናቴ በሕፃንነቴ እንዴት ጆሮዬን እንደ በላች:: የእኔ ታላላቆች ሦስቱም በተከታታይ ስለ ሞቱ ልጅ አልባ መሆኑ ያሳሰበው አባቴ ወደ ጠንቋይ ቤት ሄደና ጠየቀ:: ጠንቋዩም፣ "የሞቱት ወንዶች ናቸውና ቀጥሎ የሚወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ እንደ ተወለደ ወዲያው ሰው ባልተጠቀመበት በስለታም ምላጭ የግራ ጆሮውን ጫፍ እናቱ ሳታይ ቁረጥና በእንጀራ ጠቅልለህ ለእናቱ አብላት:: መዋጥዋን ካረጋገጥህ በኋላ «ልጅሽን በላሽው» በላት:: ያኔ በጣም ስለምትደነግጥ እነዚያን ሦስቱን ወንዶች ልጆች የገደለው በሽታ በምትደነግጥ ጊዜ ወጥቶ ይሄዳል" ይለዋል:: ልጅ ለማግኘት የፈለገውም አባቴ ልክ ጠንቋዩ እንዳለው ከእናቴ ማኅፀን እንደ ወጣሁ ወዲያው ጆሮዬን ቆርጦ ለእናቴ አበላት:: ይህ ብቻም አይደለም የሞቱት ታላላቆቼ ወንዶች ስለነበሩ ይህኛው ልጃችንም ወንድ መሆኑን ካወቀ ይገድልብናል ብለው በሴት ስም እየጠሩ፣ የሴት ልብስ እያለበሱ 10 ዓመት እስኪሆነኝ ድረስ ለመደበቅ ሞከሩ፤ እና እኔም ያደግኩት በዚህ ዘዴ መሰላቸው:: ነገር ግን ካደግኩ በኋላ አባቴም በእኔ ምስክርነት ወንጌልን ሰምቶ ጌታን ተቀብሎ ከተረዳ በኋላ የሚያድን፣ ልጅን የሚሰጥና የሚያሳድግ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ ገብቶት እንደሆነ ለመፈተን፣ የመጀመሪያ ልጄን ስወልድ፣ "ጆሮውን ልቁረጥ ወይ?" ብዬ ስጠይቀው፣ "ተወኝ ልጄ፣ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ እንጂ የእኛ አይደለምና:: ባለፈው

በአንተ በልጄ ላይ ያደረግኩትን እግዚአብሔር ይቅር ብሎ የዘላለም ሕይወት ስለሰጠኝ አመሰግነዋለሁ" አለኝ።»

አዎ፣ ልጅን በመስጠት የሚባርክና የሚያሳድግ፣ መካኒቱን የልጆች እናት የሚያደርግ፣ የልብን ፈቃድና ፍላጎት እንደ በጎ ፈቃዱ የሚያደርግ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነውና በእርሱ እንታመን። ጠንቋይ ለራሱ አያውቅምና ገንዘባችንን አንጨርስ፤ እግዚአብሔር ብቻ አዋቂ ነው። እርሱ ይሰጣል፣ እርሱም ያሳድጋል። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና!» (ፊልጵ. 2:13)

ግጥምጥም:- ልቦና ልግዛና ላቁም ኪሣራዬን፣

ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ነገር ላይሆን።

1ኛ. ዮሐ. 5:14

# መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም

የቃል ጥናት ጥቅስ፦ «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።» (ፊልጵ. 4፡6)።

ሰባኪው፡ «ብዙ ጊዜ በሕይወታችን የምንጨነቀው እምነት ሲጠፋ፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለን መታመን ሲወሰድ ነውና ለዛሬም ለነገም ለዘላለም በእግዚአብሔር ልንታመን ያስፈልጋል። እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ ገገር፣ ሁሉን የሚችልና የሚያኖር አምላክ ነው። አንዳንድ ጊዜማ በሕይወታችን የሚገርም ነገር ይሆናል። ለሌሎች ጭንቀት መፍትሔና መንገድ አሳይተን በሁሉን ቻይ ጌታ እንዲታመኑና እንዲያርፉ መክረን እነርሱንም አሳርፈን እኛ ግን አሁንም እንጨነቃለን። መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም እንደሚባለው ሲሆንብን እናያለን። ወገኖቼ፣ እግዚአብሔር እናንተ ከወፎች ትበልጣላችሁ፤ ወፎችን የሚመግብ አምላክ በአምሳሉ የተፈጠርነውን እኛንማ እንዴታ። ስለዚህ በነገር ሁሉ አትጨነቁ፣ ይልቁንም ጭንቀታችሁን አስታውቁ ይላል ጌታ።» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ።

አንድ ጓደኛዬ አንድ ቀን እንዲህ ብሎ አጫወተኝ፡ ብዙ ሠራተኞች እኛ ቤት ገብተው ትምህርት አግኝተው ይሄዳሉ። የአሁኗ ሠራተኛ ግን የተገላቢጦሽ እግዚአብሔር ትምህርት በእርሷ አስተማረን። ይገርምሃል በምንም ነገር ሁልጊዜ ስትጨነቅ አላያትም፣ ነገረ ሥራዋ ይገርማል። ባለፈው ሰሞን ያደረገችውን ሁለት ነገር ብቻ ልንገርህ። ሁላችንም ማታ ቁጭ ብለን ሳለ፣ "እሜቴ፣ ጤፍ አልቋል" ብላ አስታወቀች። ባለቤቴም፣ "ምን ነው ወሩ ሳይሞላ?" ትላታለች። "ምን ይደረግ እሜቴ፣ እንደ ጉድ ተበላ" አትላት መሰለህ ዘና ብላ። ምን ይኸ ብቻ እንደገና በነጋታው ደግሞ እንደዚሁ ሳትጨነቅ ዘና ብላ መጥታ፣ "እሜቴ፣ ቂቤም አልቋል" ትላታለች። ያለወትሮው ሁሉም ወሩ ሳይደርስ በማለቁ የተገረመችው ባለቤቴ፣ "ዘንድሮስ ጉድ መጣ ትላታለች"። "ምን ይደረግ እሜቴ፣ እንደ ጉድ ተጠጣ" ብላት አረፈችው። በሁኔታው ተገርመን፣ "ይህች ልጅ ሳትጨነቅ ከማስታወቅ ሌላ ምን ድርሻ ነበረባት። እኛ እንጨነቅ እንጂ እርሷ ለምን ትጨነቃለች? ከእኛ ጋር ካልተስማማች ከፈለገች ከእኛ ወጥታ ሌላ ቤት ትገባለች፣ ምን ያስጨንቃታል አልንና እኛም እኮ ምን ያስጨንቀናል? አስታውቁኝ ላለው ጌታችን እናስታውቃለን" ብለን ትምህርት ተማርንባት እልሃለሁ።

እውነት ነው፣ የእኛ ኃላፊነት በነገር ሁሉ ያለማቋረምረም ከምስጋና ጋር ማስታወቅ ነው። ጌታ ችግራችንን ሊያስቀግር፣ ጨለማችንን ሊያበራ፣ ተራራችንን ሊንድና ምድረ በዳችንን ሊያለመልም ታማኝ ነው። አሜን።

ግጥምጥም፦ ጭንቀቴን ሊያስወግድ ካለ ፈጣሪዬ፣

የውስጤን ነግሬው ልረፍ በጌታዬ።

ማቴ. 6፡24-34
መዝ. 62፡2

# ክፍል 11

## ስለ እግዚአብሔር ቃል

## የጨረቃ ቤት

ሰባኪው ለቤተ ክርስቲያናቸው ምእመናን ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን የዕለቱን መልእክት እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ:: «ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ ከሰው ልጆች ጋር የሚገናኘው በቃሉ ነው፤ ቃሉን ሲናገር ያሳርፋል፣ ይመራል፣ ይመልሳል፣ ይፈውሳል:: ቃሉ ኃይል አለው:: ስለዚህ እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምሯችሁን ሰዎች በጥንቃቄ በማስተዋል ስሙ፣ ሰምታችሁ የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ሰሚዎች ብቻ አትሁኑ፣ ወይም በአንድ ጆሮ ሰምታችሁ በሌላኛው ጆሮአችሁ አታፍስሱ:: ደግሞ ልንገራችሁ ሰይጣን ዲያብሎስ የተዘራውን ዘር ለመልቀም ሁልጊዜ አይተኛምና ንቁ አስተውሉም:: የሰማነውን እውነተኛውን ቃል አጥፍቶ ያልሰማነውን ያሰማናልና ተጠንቀቁ::» በማለት በራሳቸው ቤት የገጠማቸውን ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ:: ሁልጊዜ ማታ ማታ ከቤተሰቤ ጋር የቤተሰብ ጸሎት አድርገን ስለምንተኛ ቃሉን ከቤተሰቤ ጋር እንማር ነበር:: በዕለቱም፣ «ይህ ቤት የብርሃን ቤት ነው» በሚል ርእስ ቃሉን አስተምር ነበር:: ልጆቼም ባለቤቴም ሁሉም በደስታ ይሰሙ ነበር:: እኔም በዚህ ቤት ውስጥ የጨለማ ሥራ የሆኑትን ክፋትን፣ ተንኰልን፣ ምቀኝነትን፣ ስድብን፣ መራርነትን፣ ሐሜትን፣ ንዴትን፣ ቁጣን፣ ግብዝነትን ሁሉ አስወግደን ልንመላለስ ይገባል:: ምክንያቱም ይህ ቤት የብርሃን ቤት ነው እያልኩ ማስተማር ጀመርኩ:: ታዲያ በመካከል ሁሉን ስመለከት አንዷ ልጄ በሥጋዋ እንጂ በአሳቧ እዚያ እንዳልነበረች በሁኔታዋ ስለተረዳሁ ስሟን ጠቅሼ፣ «ይህ ቤት የምን ቤት ነው?» ብዬ ጠየቅኋት፣ እርሷም ከሄደችበት በአሳብ በመባነን በድንገት፣ «የጨረቃ ቤት ነው» አለችኝ:: በዚያን ሰሞን በአካባቢውና በቴሌቪዥን የሰማችው ይህ የጨረቃ ቤት ጉዳይ ትዝ ብሏት::

አንባቢ ሆይ፣ ሰይጣን ከእግዚአብሔር የሰማኸውን ቃል ወስዶ ከዓለም የሆነውን ያሰማሃልና አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ:: የእግዚአብሔር ቃል ሲነገር በሙሉ ልብ ሰምተን በሙሉ ልብ እንድንተገብር ጌታ ይርዳን ::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ::»

ግጥምጥም:- በቃሉ እንዳትኖር ወጥቷል የሚነጥቅ፣
ክርስቲያን ወገኔ አእምሮህን ጠብቅ::

ማቴ. 13:14
ኤፌ. 4:31

# የሌባ ዓይነ ደረቅ

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር ሊደርስብን ያለውን ነገር እንድንጠነቀቅ አስቀድሞ በቃሉ በባሪያዎቹ በኩል ይናገራል፤ ያንን ሰምቶና አስተውሎ እንደ ጌታ ፈቃድ ያልሆነውን መተው፣ የጌታን ፈቃድ ደግሞ መፈጸም መልካም ነው:: ቃሉም እንዲህ ይላል:: "አሁንም:- ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ ተመልከቱ፣ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና::" (ያዕ. 4:13):: አዎ፣ ወገኖች፣ መሄድ፣ መነገድና ማትረፍ የሚቻለው ጌታ ሲፈቅድና ምሪትም ሲሰጥ ብቻ ነው:: በፈቃዳችን ፈቃዱን ጥለን ብንሄድ ግን በማትረፍ ፈንታ ኪሳራ፣ በዚያች ከተማ በመኖር ፈንታ ሞት ነው የሚጠብቀንና ፈቃዱን እንወቅ» ለሚለው መሠረታዊ የክርስትና ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

የአንድ ሰውን ቤት በሌሊት እዘርፋለሁ ብሎ በር ሰብሮ ለመግባት የሞከረ አንድ ሌባ ነበረ:: ታዲያ የቤቱ ባለቤት ሁልጊዜ ቤቱን ነቅቶ የሚጠብቅ ነበርና በዚያ ሌሊት ሌባው በር ለመስበር ሲጎረጉር ሰምቶ ጦሩን ይዞ ከበሩ ሥር ሆኖ ይጠባበቅ ነበር:: ሌባውም ከብዙ ትግል በኋላ እንዳሰበው ለመፈጸም በሩን ሰብሮ እንደ ገባ ድንገት ሳያስበው የቤቱ ባለቤት በያዘው ጦር ሆዱን በኃይል ይወጋዋል:: በዚህ ጊዜ ሌባው ያሰበው ቀርቶ ያላሰበው ስለደረሰበት በጣም ተናድዶ ሆዱን በእጁ ይዞ ለባለቤቱ እንዲህ አለው፣ «በጦር የወጋኸኝ መስሎሃል እንዴ፣ አልወጋኸኝም» አለ:: የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ እንደተባለው፤ በዚህ ጊዜ ባለቤቱ በደንብ እንደ ወጋው ያውቃልና እንዲህ ብሎ መለሰለት፣ «አሁን ሂድ፣ ውጤቱን በኋላ ታገኘዋለህ» አለው::

አንባቢ ሆይ፣ እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈስ የሚመራንን ትተን በእኛ ፈቃድና ስሜት ብንጓዝ የከፋ ሁኔታ ይገጥመናልና እንመለስ:: ውጤቱም እንደዚህ ሌባ የኋላ የኋላ የሚያጠፋ ይሆናልና ለሥራችንም ሆነ ለትዳራችን፣ ለንግዳችንም ሆነ ለመኖሪያችን እንደ እግዚአብሔር አምላካችን ፈቃድና እንደ ቃሉ፣ እንደ መንፈስ ቅዱስም ምሪት እንድንኖር ቀሪ ዘመናችንን ጌታ ይባርክ:: አሜን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል» (ያዕ. 4:15)

ግጥምጥም:- በፈቃዴ ሄጄ አልተሳካምና፣

ጌታ ያለው ይሁን ከእንግዲህ በኋላ::

ኤፌ. 5:17
የሐዋ. 4:19

# እኔም ዜሮ ነኝ!

አንድ ቀን ወደ ክፍለ ሀገር ለአገልግሎት እየሄድን ነበር:: አውቶቡሱ ግጥም ብሎ ሞልቷል:: ከአዲስ አበባ ከተማ የተወሰኑ ኪሎ ሜትሮች ከተጓዝን በኋላ ግማሹ ተረጋግቶ የሚሄድበትን ያስባል፣ ግማሹ ከጐኑ ካለው ሰው ጋር ያወራል:: በዚህ መሐል ሾፌሩ ድምፁን ከፍ አድርገው ዘፈን ከፈቱ:: የሚገርም ዘፈን ነበር! እንደዚህ ያለ ዘፈን ከዚህ ቀደም ሰምቼ አላውቅም፣ እስካሁንም ሌላ አልሰማሁም:: እንደዚህ ይላል፣ «ይገርማል ዘንድሮ ይደንቃል ዘንድሮ፣ ሁሉም ዜሮ ዜሮ፣ ሁሉም ዜሮ ዜሮ»:: በዚህ ጊዜ ከአጠገቤ የተቀመጡት አንድ ሰው ከረባታቸውን እየነካኩ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው፣ «ሾፌር የዘፈኑን ድምፅ ከፍ አድርገው፣ እኔም ዜሮ ነኝ» አሉ:: ወዲያው የጌታ መንፈስ፣ «አንተ ግን ዜሮ አይደለህም» አለኝ::

«አዎ፣ እኛ ክርስቲያኖች በእውነት ይህንን ከልባችን ልንገነዘብ ይገባል:: ሰማይና ምድርን የፈጠረ ጌታ በእኛ ውስጥ ሳይንቀን አድሯልና ራሳችንን ከሚጠፋው ዓለም ጋር እያወዳደርን መናቅ የለብንም:: ምንም እንኳ ዛሬ ብዙ ሀብት፣ ገንዘብ፣ ጥሪት ወይም ስም፣ ዝናና ውበት የሌለን ብንመስልም፣ ከዚህ ሁሉ በላይ የሆነና የከበረ ጌታ ግን በእኛ ውስጥ ስላለ የከበርን ነንና ከሚጠፋው ባሻገር የማይጠፋውን እንመልከት:: የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሐዋርያት ጴጥሮስና ዮሐንስ ይህንን በሐዋ. *ሥራ* 3:6-7 ሲያረጋግጡልን፣ "ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው:: በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቁርጭምጭምቱ ጸና፣ ወደ ላይ ዘሎም ቆመ::" አዎ፣ ለዚህ ሽባ ሰው ብርና ወርቅ ቢሰጡት ኖሮ ቁርጭምጭሚቱ ሊጸናና ሊፈወስ፣ ዘሎም ሊቆምና ሊመላለስ ባልቻለም ነበር:: እንግዲህ በውስጣችን ያለው ኃይል ከብርና ከወርቅ፣ ከስምና ከዝና እጅግ የበለጠ ነውና ይልቅ በሙሉ ልብ ተነሥተን እንጠቀምበት:: ክርስቶስ ያለው ሰው ጐዶሎ ሳይሆን ሙሉ ነው:: ዓለም እንደ ትንሽና ምንም እንደሌለው አድርጋ እንደምትንቀው ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ነው::»

*የቃል ጥናት ጥቅስ* «... ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፣ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፣ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ::» (ኢሳ. 66:2)::

አዎ፣ ቅዱሳን ሆይ፣ በውስጣችን የእግዚአብሔር መንፈስ ስላለ እኛ ዜሮ አይደለንም፣ ወይም የቀን ጨለማ የወረሰን በባዶነት የተሞላን አይደለንም:: በመሆኑም፣ ራሳችንን በቅድስና ይዘን ግራ ወደገባቸውና «ሁሉ አለን፣ ምንም አያስፈልገንም» ብለው ነገር ግን በዜሮ ሕይወት ወደሚመላለሱት ሄደን ሙሉውን ወንጌል ማሳየትና መናገር እንድንችል ጌታ ይርዳን::

*ግጥምጥም:- ምንም እንደሌለህ ራስህን ሳትንቅ፣*
*ከሙሉው ጌታ ጋር አንተነትህን አጣብቅ::*

ዘፍጥ. 39:9
1ኛ ቆሮ. 3:16-17

# ኢየሱስ ሳሎን ቤት ነው ያለው

ልጅቷ መለስተኛ መዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ቤት ትማራለች:: ቤተሰቦቿ ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ቢሆንባቸውም፣ በመጠን እየኖሩ ልጃቸውን ገና ከልጅነቷ ትምህርት ለማስተማር ወስነዋል:: ልጅቷ ታዲያ የቤተሰቧ ኑሮ ዝቅተኛነት ስለማይገባት በትምህርት ቤት ሌሎች ልጆች ሲበሉና ሲለብሱ ያየችውን ሁሉ ለራሷም በመመኘት ከትምህርት ቤት መልስ ሁልጊዜ ማታ ማታ፣ «ይህንን ግዙልኝ፣ ይህንን ምግብ ሥሩልኝ» እያለች ከአቅማቸው ጋር የማይሄደውን ሁሉ ታዝዛለች:: አባትና እናት ልጃቸው ገና በጨቅላ አዕምሮዋ እንዳትጎዳ በማሰብ አንዳንድ ከገቢ ምንጫቸው ጋር የማይመጣጠን ነገር ሁሉ ያደርጉላታል:: አንድ ቀን ያላት ጫማ ሳያልቅ የሃብታም ልጆች በውድ ዋጋ የተገዛ ጫማ አድርገው ስላየች ብቻ እንዲገዛላት እንደተለመደው ማታ ለአባቷ ጥያቄዋን አቀረበች:: አባትም ከአቅማቸው በላይ እንደሆነ በመግለጽ «ለአባባ ኢየሱስ እንንገረው፣ እርሱ ይገዛልሻልና ነይ እንጸልይ» ብለው አንገታቸውን ሲደፉ አቋረጠችና፣ «ታዲያ፣ መኝታ ቤት ነው የምንጸልየው? አይደለም::» አለች:: «ለምን?» አሏት አባቷ:: «ኢየሱስ ያለው እኮ መኝታ ቤት ሳይሆን ሳሎን ቤት ነውና እዚያ እንሂድ» ብላ እጃቸውን እየጎተተች ሳሎን ቤት ወደተሰቀለው በተለምዶ ኢየሱስ ተብሎ ወደሚባለው ሥዕል ይዛቸው ሄደች:: አባቷም መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ሁሉ ቦታ መገኘቱን እንዳታውቅ ባደረገው ሥዕልና ይህንንም ሥዕል በውድ ዋጋ ገዝተው ቤታቸው በማምጣታቸው እየተናደዱ እንዲገባት፣ «ኢየሱስ ሳሎን ቤት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ቦታ ይገኛል:: እንግዲህ እንዳልሽው ኢየሱስ ጫማ እንዲገዛልሽ ነይ እንጸልይ» አሏት:: በድጋሚ እርሷም ትንንሽ ጣቶቿን ወደ ሥዕሉ እየጠቆመች፣ «ይኸኛው ኢየሱስማ ጫማ ሊገዛልኝ አይችልም:: ተመልከት አባባ፣ ለራሱም እንኳ ቆንጆ ጫማ አላደረገም» ብላቸው አረፈች::

አዎ፣ ወገኖቼ፣ የእኛ አምላክ በግርማውና በክብሩ ሰማይና ምድርን የሞላ፣ ቦታና ጊዜ የማይወስነው ጌታ ነው እንጂ በፍሬም (በፎቶ ማስቀመጫ) ውስጥ ተወስኖ የተቀመጠ አይደለምና ይህንን ጣዖት እናስወግድ:: በየቤቶቻችን የሰቀልናቸው ሥዕሎች እኛን የፈጠረው አምላክ ወኪሎች ሳይሆኑ የተፈጣሪው የእጅ ሥራ የሆኑ ጣዖቶች ናቸውና ለራሳችንና ለቀሪው ትውልድ እንጠንቀቅ::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል::» (ዮሐ. 4:24)

ግጥምጥም:- ለምን ታመልካለህ ለአንተ የማይበጀውን፣
ፈጣሪህን ትተህ የተፈጠረውን::

ዘፀ. 20:3-4
ኢሳ. 44:9-17

# በኤፌሶን ይገፎዎታለሁ

*«ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፣ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ» (ኤፌ. 5:33)*

ቄሱ ሁለቱን የጋብቻ ቃል ኪዳን ፈጻሚዎች በፊታቸው አቁመው ወደ እነርሱ እየተመለከቱ፣ «ዛሬ እናንተን በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባኤ ፊት ቃል እንድትገቡ ከመጠየቁ በፊት፣ የምትገቡትን ቃል ወደፊት በኑሮአችሁ እንደምትፈጽሙትና እንደገባችሁት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደምትኖሩ ካረጋገጣችሁልኝ በኋላ ነው አሉአቸው::» እነርሱም በአንድ ላይ፣ «በጌታ ጸጋ ዛሬ በምንገባው የጌታ ቃል ኪዳን መሠረት እንኖራለን» አሉአቸው:: ቄሱ ባርከዋቸው፣ «ይህን ያልኩበት ምክንያት ዛሬ ሰዎች መድረክ ላይ በቅዱሱ እግዚአብሔርና በቅዱሳኖች መካከል የፈጸሙትን ቃል ኪዳን ነገ በትዳራቸው ውስጥ ለመተግበር ሲቸገሩ ስለማይ ነው» ብለው ይህንን በተግባር የተገለጸ ምሳሌ አስከትለው ለተጋቢዎቹና ለጉባኤው ተናገሩ::

«ልክ እንደ ዛሬው እንደ እናንተ ከዛሬ 25 ዓመት በፊት የተጋቡ ባልና ሚስት ነበሩ:: ሙሉ ደስታ ግን በትዳራቸው አይታይም:: አንዱም የሚያጋጫቸው ባልየው ለቤተሰቡ ጊዜ አለመስጠቱ ነው:: አንድ ቀን ያለወትሮው ባል በጊዜ ወደ ቤቱ መምጣቱ ሚስቱን አስደስቷት ወደ ፊት አነሣቸዋለሁ የምትላቸውን አጀንዳዎች ሁሉ እያነሣች ሲነጋገሩ፣ አንዳንዱ አጀንዳ ጠንካራ ነበርና ከጭቅጭቅ አልፈው ባልን ዱላ እንዲመዞ አደረጋቸው:: ስለሆነም ለመማታት ባል ዱላቸውን መዝዘው በሚስታቸው ላይ ሊያሳርፉ ሲሉ፣ ሚስት የዛሬ 25 ዓመት በሠርጋቸው ላይ የገቡትን ቃል ኪዳንና ከኤፌሶን የተሰበከውን ቃል ጮክ ብለው ማስታወስ ጀመሩ:: እንዲህ እያሉ፣ "ኧረ በኤፌሶን ይገፎዎታለሁ! ኧረ በኤፌሶን ይገፎዎታለሁ!" ባል ግን የገቡትን ቃል ኪዳን ረስተውና ቃሉን ተላልፈው ሚስታቸውን ደበደቡ:: ወገኖቼ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ ማለት በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ፣ የሥጋ ሥራ የተደፈነበት ማለት ነውና ሁላችንም በዚህ መሠረት ትዳራችንን እንድንመራ ፈጣሪ ያግዘን» ብለው ቃል ኪዳን ማስፈጸማቸውን ቀጠሉ::

አዎ፣ አንባቢ ሆይ፣ አንተስ እንደ እግዚአብሔር ቃል በፍቅርና በመስማማት የክርስቶስ መልካም ምስክር ሆነህ ትዳርህን እየመራህ ነው? በእግዚአብሔር መንፈስ የተጀመረ ፍቅር በእግዚአብሔር መንፈስ እየታደሰ ይሄዳል:: እንደገባነው ቃል ኪዳንና በእጃችን እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወታችንንና ትዳራችንን እንድንመራ ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ቃሉን ሰምተህ በቃሉ ኑር፣
በራስህ ድካም እምላክን አታማር::

| |
|---|
| ፊልጵ. 2:1-5 |
| ኤፌ. 6:10-13 |

## በውሻ የተበላው ስብከት

**የቃል ጥናት ጥቅስ፡-** «ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና::» (2ኛ ጢሞ. 4:2)

መጋቢው በቤተ ክርስቲያናቸው የአገልጋዮች ኅብረት ቀን እንደዚህ እያሉ ሰባኪዎቹን ማስተማርና መምከር ጀመሩ:: «እናንተ ሰባኪዎች፣ በጊዜውም አለጊዜውም ቃሉን ለመስበክ የተዘጋጃችሁ መሆን አለባችሁ:: ሁልጊዜ የምታስተምሩት የእግዚአብሔርን ቃል ቢሆንም እንኳ፣ ቃሉ የሚለውን በትክክል ማለታችሁን እርግጠኛ ሁኑ:: እንዲሁም ቃሉ የሚለውን ለሕዝቡ ለማቅረብ የተመረጠ የስብከት አቀራረብ ዘዴ ተጠቀሙ:: ረጅም ሰዓትና ረጅም ነጥቦች/ አሳቦች/ ይዛችሁ ለመስበክ ብትሞክሩ፣ የሰው አእምሮ ውስን ነውና ሁሉንም መልእክታችሁን ማስተላለፍ አትችሉም:: የእግዚአብሔርንም ሕዝብ አድክማችሁ ጊዜውን በከንቱ ትጨርሳላችሁ:: ለዚህም ተጠያቂዎች ናችሁ:: ስለዚህ ስሙኝ ምክሬ በ45 ደቂቃ የስብከት ጊዜ ከ3 ወይም ከ4 ነጥቦች በላይ ማስተማር አትችሉም የሚል ነው:: ሰዎች ነጥቦች ሲበዙ የመጀመሪያውን እየረሱ ስለሚሄዱ ተጠንቀቁ፣ ጊዜም አይበቃኝም ብላችሁ ምንም ለሕዝቡ ፈውስ የሚሆንና ተጨባጭ የሆነ ትምህርት ሳትሰጡ ሕዝቡን በስሜት ብቻ በአየር ላይ አውጥታችሁ እንዳትለቁ ተጠንቀቁ:: ለዚህ ሁሉ መጸለይ፣ ማንበብና የስብከት ዘዴዎችን ሁሉ ማወቅና መጠቀም አለባችሁ:: አለበለዚያ በእግዚአብሔርም ሆነ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት አግኝታችሁ ከመወደድ ይልቅ ትሰለቻላችሁ፣ ትጠላላችሁም::» ይህንንም አስመልክተው መጋቢው ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

ውጭ አገር በረጅም ስብከቱ የተነሣ ሰዎች የማይቀበሉት አንድ መጋቢ ነበር:: እና ሁልጊዜ በሰበከ ቁጥር ከ12 ነጥቦች በታች ተጠቅሞ አያውቅም:: በዚህም ሕዝቡ ሰልችቶታል:: ተደጋግሞም ተነገረው፣ ሊያስተካክል አልቻለም:: አንድ ቀን ግን አዲስ ክስተት ሆነ:: እንደተለመደው መጋቢው ሊሰብክ ቆሞ ሳለ እንዲህ ብሎ በኀዘን ቃል ተናገረ፣ «ዛሬ በፊታችሁ በጣም አዝኜ ነው የቆምኩት:: ለስብከቴ ከተዘጋጀኋቸው 12 ነጥቦች ውስጥ 9 ነጥቦቼን ውሻዬ በልታብኛለች:: ስለዚህ 3ቱን ብቻ ተመልክተን በጊዜ እንጨርሳለን» ከማለቱ አዳራሹ በሙሉ በደስታ ጭብጨባውን አስተጋባ:: መጋቢውም በሦስቱ ነጥቦች ብቻ ሰብኮ ጉባኤውን በጊዜ አሰናበተ:: መጨረሻ ላይም አንድ ከሌላ

ቤተ ክርስቲያን የመጣ እንግዳ ክርስቲያን ሰውዬ ወደ መጋቢው ሄደና፣ «የእርስዎ ውሻ ባደረገችው ተደስቻለሁ:: የእኔም ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንደዚሁ ከ12 ነጥቦች በታች አይሰብክምና የእርስዎ ውሻ ቡችላ ካላት ቢሰጡኝና ይገፍለት ብሄድ ግሩም ነው» ብሎ ጠየቃቸው::

አዎ፣ አገልጋዮች ሆይ ሕዝቡን፣ ጸጋውንና መድረኩን የሰጠን እግዚአብሔር ነውና እርሱን አስደስተን ሕዝቡንም በሚገባው መጠን አስተምረን የታማኝ ባሪያን ሽልማት ለመቀበል እንዘጋጅ:: በዚህም ሩጫችንን እንድንጨርስ ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- የእግዚአብሔርን እውነት በግልጽ ተናገር፣

ዋጋ ታገኛለህ በላይኛው አገር::

2ኛ ቆሮ. 6:1-7
2ኛ ጢሞ. 4:5

## ለካስ ለበጎ ነው!

**የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» (ሮሜ 8:28)**

ሰባኪው፣ «ለእኛ እግዚአብሔርን ለምንወድ ሰዎች የሚደርስብንንና የደረሰብንን ነገር ሁሉ ብንመረምረው ለበጎ ነው፤ ለጥቅማችን ነው:: ወንጌል የበለጠ እንዲሰፋ እግዚአብሔር የከበረ ሥራውን በሕይወታችን ለመግለጽ ነው እንጂ እኛን ስለ ጠላን ወይም ለክፉ ነገር ከመጀመሪያው የተመደብን ሆነን አይደለም:: ወገኖቼ፣ እግዚአብሔር ከማዕበሉ ባሻገር ሰላም አለው፣ ከኀዘን ባሻገር ደስታ አለው:: ከለቅሶ ባሻገር ሳቅ አለውና እንታገሥ:: በራሳቸው በጎ ያልሆኑትን ነገሮች እግዚአብሔር ለበጎ ይለውጣቸዋል:: ወይም ዛሬ ችግሬና መስቀሌ ብለን የምንጠራቸው ነገሮች ሁሉ እኛን ለመሥራት እግዚአብሔር የላከልን ወዳጆቻችን ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ ስንገፋ ደስ ይበለን፣ እግዚአብሔር አብሮን አለ:: ዛሬ እየደረሰብን ያለው ጉዳይ ባይገባንም እንኳ እንጽና፣ ነገ ለፈውስ ለደስታና ለደኅንነት ሆኖ እናገኘዋለን::» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

«አንድ በሚደርስበት ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ማለት የተለማመደ አማኝ ወደ ሩቅ ሀገር ለመሄድ የተሳፈረበት አውቶቡስ በረሃ ላይ ይበላሽና ይቆማል:: እርሱም ቶሎ መሄድ ስላለበት ወደ መንገዱ ወጣ ብሎ ሌሎች መኪናዎችን ይጠብቃል፣ ለትብብር እጁን ሲዘረጋ አንድ ትንሽ መኪና ይቆምለታል:: ከፍቶ ይገባና ካመሰገነ በኋላ፣ "አየህ፣ ይህ አውቶቡስ የተበላሸው ለበጎ ነው:: እኔ በጊዜ እንድደርስ ይህችን ትንሽና ፈጣን መኪና አዘጋጀልኝ" ይለዋል:: አባባሉ ያልገባው አማኝ ያልሆነው ሰውዬም ዝም ብሎት መንዳቱን ቀጠለ:: ትንሽ እንደ ተጓዙ የመኪናው ጎማ ፈነዳና ቆሙ:: በብዙ ድካም ጎማ ተቀይሮ ለመሄድ ሲገቡ፣ አሁንም፣ "አየህ፣ ጎማው የፈነዳው ለበጎ ነው:: እኛም መኪናዎም እንድናርፍ ነው" ብሎ ሊያጽናናው ቢሞክር፣ አሁንም ሾፌሩ በውስጡ ከመጀመሪያው ይልቅ ተቆጣ:: በበረሃው ብዙ ረጅም ርቀት እየተጓዙ እያለ ድንገት መኪናዋ ትበላሽና ትቆማለች:: ሾፌሩም እርሱም ወርደው ኮፈን ተከፍቶ ሾፌሩ መካኒክም ስለሆነ ይሠራትና የሞተሩን ክዳን ወርውሮ ኮፈኑን ሲዘጋ ሳያውቅ አውራ ጣቱ ላይ ይጥለውና የሾፌሩ አውራ ጣት ይቆረጣል:: በዚህ ጊዜ እየጮኸ ሳለ አማኙ፣ "ይህም ቢሆን ለበጎ ነው" ይለዋል:: በዚህ ጊዜ ሾፌሩ በጣም ስለ

ተበሳጨ ያንን አማኝ በረሃ ውስጥ ትቶ መኪናውን ይዞ በረረ:: ብዙም ፈቅ ሳይል ሽፍቶች ያገኙታል:: ያለውንም ከዘረፉ በኋላ ለአመጣላቸው አምላክ መሥዋዕት እንዲሆን ሊያርዱት ሲመካከሩ አውራ ጣቱ በደም ተጨመላልቆ ያዩታል:: በዚህ ጊዜ፣ «አይ፣ ለአምላካችንማ አካለ ጎዶሎ መሥዋዕት አናቀርብም» ብለው ይለቁታል:: በዚህ ጊዜ ያስተውልና ወደ ኋላ ተመልሶ እዚያ አማኝ ጋ ይደርስና አውራ ጣቴ የተቆረጠው ለካስ ለበጎ ነው፣ አንተንም እዚህ ትቼ መሄዴ ይህም ለበጎ ነው:: ብትሄድ ኖሮ ታርደህ ነበር ይለዋል::»

አዎ፣ ወገኖቼ፣ በሕይወታችን እግዚአብሔር አውቋቸው የሚፈጸሙት ነገሮች ሁሉ ለጊዜው ቢያስጮኹን፣ ቢያደሙንና ባይመቹንም ነገር ግን ነገ ለበጎ ሆነው ይጠቅሙናልና እንታገሥ:: ይህንንም እንድናስተውልና እንድንኖርበት እግዚአብሔር ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- የጊዜው መከራ ቢጎረብጠኝም፣
ነገር ሁሉ በጎ መሆኑን አልስትም::

| |
|---|
| ዘፍጥ. 50:20 |
| ዮሐ. 9:1-3 |
| ፊልጵ. 1:12-14 |

# ሚስቴ ሞገሴ ናት!

የቃል ጥናት ጥቅስ: *«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው...» (ዕብ. 4:12)*

ሰባኪው፣ «ይህ ምድር ሁኔታዎች የሚፈራረቁበት ምድር ነው:: ደስታ እንዳለ ሁሉ ኃዘንም አለ፤ ጥጋብ እንዳለ ሁሉ ረሃብ አለ፤ ነጻነት እንዳለ ሁሉ ባርነት አለ፤ ማግኘት እንዳለ ሁሉ ማጣትም አለ:: ታዲያ በዚህ ሁሉ ክብርን ለጌታ እየሰጠን እንድንኖር የሚያደርገን የእግዚአብሔር ቃል ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ከላይ በገለጽኳቸው ሁኔታዎች ሁሉ መጽናኛችን ነው:: ልብ በሉ፣ በእነዚህ እና በሌሎችም ሁኔታዎች ሁሉ ስታልፉ ቃሉን ለእናንተ የሚያመጣውን መንፈስ ቅዱስን ስሙ፣ ንቁዎችም ሁኑ:: እግዚአብሔር ልጆቹን በቃሉና በመንፈሱ ያጽናናል:: ሰይጣን የእኛን ደስታ ስለማይወድ፣ ደስታችንንና ሰላማችንን ለመውሰድ ጥቃቅን ችግሮችን ሁሉ አጉልቶ ያሳየናል:: በዚያን ጊዜ የጠላትን ልብ ልንረታ የምንችለው፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ልባችንና አእምሮአችን የሚያመጣውን ቃሉን በንቃት ተቀብለን በእምነት ስንወነጭፍ ነው» ለሚለው መልእክታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ::

«ሁላችንም እንደምናውቀው የሰርግ ቀን፣ የደስታና የፌሽታ ቀን ነው:: ለእኔ ግን የእግዚአብሔር ቃል በመንፈሱ አማካይነት እስኪመጣልኝ ድረስ አልነበረም:: የምሬን ተበሳጭቼ ነበር:: የተበሳጨሁበትንም ምክንያት በደንብ ሳውቀው፣ 'በእውነትም ሰይጣን የክርስቲያኖችን ደስታ አይወድም' አልኩኝ፣ ታሪኩ እንዲህ ነው:: በሙሽራ መኪና ከሙሽራዬ ጋር እየሄድኩኝ ሳለ፣ ሰርግ በዘመኑ ብርቅ ነበርና ሰዎች ሙሽራይቱን እያዩ ያደንቁ ነበር:: ሁሉም በእርሷና በእኔ የመኪና መስኮት በኩል ዝቅ እያሉ፣ እስቲ ሙሽራዋን ልያት፣ እስቲ ሙሽራዋን ልያት' ይላሉ:: ይህ አባባል እኔን አበሳጨኝ፤ "አንድም ሰው እንኳ ተሳስቶ፣ እስቲ ሙሽራውን እንየው አይልም እንዴ?" አልኩኝ:: ወዲያው የእግዚአብሔር መንፈስ ቃሉን ወደ እኔ አመጣ፣ "ሚስትን ያገኘ በረከትን አገኘ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን ይቀበላል" (ምሳሌ 18:22):: ለካ ይህቺ ከጎኔ የተቀመጠችው ሞገሴ ናት እና በሞገሴ እንዴት እቀናለሁ፤ ሰይጣን እግዚአብሔር ይገሥጽህ፣ እርሷ ሞገሴ ናት አልኩኝ:: ከዚያ በኋላ ሰዎች፣ 'እስቲ ሙሽራዋን እንያት' ሲሉ፣ "ሞገሴን እይዋት" እያልኩኝ ማሳየት ጀመርኩ::»

አዎ፣ የእግዚአብሔር ቃል ሲመጣ ይፈውሳል፣ መንፈስ ቅዱስ በጊዜው ላለንበት ሁኔታ የሚያመጣውን ቃል በነቃ መንፈስ ሆነን እንቀበል፤ በእኛ ሆኖ ሥራውንም እንዲሠራ ልባችንን እንክፈት::

| |
|---|
| ዕብ. 4:16 |
| ቲቶ 3:8 |

ግጥምጥም:- በየዕለት ኑሮዬ ችግር ሲያጋጥመኝ፣
እግዚአብሔር በቃሉ ይመጣል ሊያጽናናኝ::

# መሃይሙ አስረኛ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል::» (ዮሐ. 16:8)

«በዚህ ምድር - ላይ ያለነው ለሁለት ነገሮች ነው:: አንደኛ፣ እግዚአብሔርን ታምነን እርሱን ብቻ እንድናመልክ:: ሁለተኛ፣ በሕይወታችንና በአንደበታችን ለዓለም ወንጌልን ለመመስከር ነው:: ይህ በደንብ ከገባን አንዱን ጥለን ሌላውን ብቻ የመያዝ አዝማሚያ አይታይብንም:: ዛሬ ለሰዎች ወንጌልን መመስከር ችላ ብለናል:: ለምን? ምናልባት የእኔ ምስክርነት ሰዎችን ስለለወጣቸውና ጌታን ስለማይቀበሉ መተው አለብኝ የሚል ከሰይጣንና ከሥጋ የመጣ ተስፋ አስቆራጭ ምክንያት ይሆናል:: ወገኖቼ አንድ እውነት ተረዱ:: የእኛ ድርሻ መናገር እንጂ የሰውን ልብ መለወጥ አይደለም:: ወንጌሉን አብርቶ የሰውን ልብ መለወጥ የሚችል ሕያው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው:: የእርሱን ወቀሳና ኃይል ማንም ሊቋቋም አይችልም:: እስቲ አንድ የተፈጸመ ምሳሌ ልንገራችሁ::» ብለው ሰባኪው ቀጣዩን ምሳሌ ለጉባኤው ተናገሩ::

አንድ አማኝ የታሠረ ዘመዱን ለመጠየቅ ወደ ወኅኒ ቤት ይሄዳል:: በዚያውም ለእሥረኞች ለመስጠት ሁለት መጽሐፍ ቅዱሶችን ይዞ ይሄዳል:: የሚጠይቀውን ሰው ፖሊሱ እስኪጠራለት ድረስ ወደ አጥሩ ጠጋ ብሎ ከውስጥ ግንብ ሥር ቆም ብለው ላሉ ሁለት እሥረኞች መጽሐፍ ቅዱሶቹን ያወጣና፣ «እነዚህን ለእናንተ ስጦታ ለመስጠት እፈልጋለሁ:: ውሰዱና አንብቡ» ሲላቸው፣ አንደኛው፣ "እንቢ" አለ:: ጭራሽም፣ "ጴንጤ መሆን አልፈልግም» ብሎ ተናገረ፣ ተቆጣም:: ሁለተኛው ደግሞ፣ «ጴንጤ የመሆን ወይም ያለመሆን ጉዳይ ሳይሆን፣ ስጦታ ብሎ ሲሰጠን እንደ አገራችን ባህል አመስግነን ነው መቀበል ያለብን» ብሎ ጓደኛውን በመቆጣት ለራሱ ብቻ፣ «አንዱን መጽሐፍ ቅዱስ ለእኔ ስጠኝ» ብሎ ተቀበለ:: በውስጡ ምን እንደሚል ማወቅ ፈለገ:: ግን ማንበብ አይችልም:: እምቢተኛው ጓደኛው ግን ይችላልና ማታ ለአንተ ሳይሆን ለእኔ አንብብልኝ ብሎት ሰጠው:: ይህም ሰው ድንገት የከፈተው 12 ዓመት ደም የፈሰሳትን ሴት ፈውስ ጉዳይ የሚያወሳውን ክፍል ነበርና ለሰውዬው ያነብለት ጀመር:: ነገር ግን በንባቡ መሃል ቀና ብሎ አንብብልኝ ያለውን ጓደኛውን ሲያየው ለካስ እንቅልፍ ወስዶታል:: በዚህ ጊዜ ይህ ሰው እንዳያነብ ስሚው

ተኝቷል። እንዳያቆም 12 ዓመት ደም የፈሰሳት ሴት ታሪክ ገርሞታልና መጨረሻው ድረስ አነበበ። ሳያውቀውም እንባው በጉንጩ ላይ ፈሰሰ። ጓደኛውንም ቀሰቀሰ፣ «በርግጥም ኢየሱስ ጌታ ነው። አዳኝ ነው።» ብሎ ተናገረ። ሁለቱም የሕይወታቸው ጌታ አድርገው ኢየሱስን አመኑት /ተቀበሉት/።

አዎ፣ የሰውን ልብ ሊለውጥ የሚችለው ሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ እና ቃሉ ናቸው። የእኛ ድርሻ መናገር ነው። ጌታ ድርሻውን መወጣት ይችልበታል። ስለዚህ በቤታችን፣ በጎረቤታችን፣ በአካባቢያችንና በሥራ ቦታችን ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠንን የተከፈተ በር ሁሉ ተጠቅመን ሰላምና ሕይወት የሚሰጠውንና የታሰሩትን የሚፈታውን ወንጌል እንድንናገር ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም:- በአሉባልታ ወሬ ዓይን ከማወጣ፣
ቃሉን በመመስከር ድርሻዬን ልወጣ።

| |
|---|
| ዮሐ. 16:13 |
| ዕብ. 4:12 |

## ክፍል 12

## ግብዝነት ስለሌለበት እውነት

# ገመድ ሰርቄአለሁ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል::» (ምሳሌ 28:13)::

የቤተ ክርስቲያኒቱ የንስሐ ፕሮግራም ላይ እንዲሰብኩ የተጋበዙት ቄስ እንዲህ እያሉ ስለ እውነተኛ ንስሐ መስበክ ጀመሩ:: «እውነተኛ ንስሐን እግዚአብሔር ይወዳል፤ በእግዚአብሔር ፊት የሠራችሁትን ሁሉ ምንም ሳትደብቁና ሳታፍሩ ተናዘዙ እንጂ ለሰው ለመናገር እንደምታፍሩ ለእግዚአብሔር ለመናገር አትፈሩ:: ይልቁንም ስለ ኃጢአታችሁ እፈሩና አስወግዱት እንጂ:: በደፈናው፣ "የሰረቅሁትን ነገር ይቅር በለኝ" ከማለት፣ "የሰረቅሁት ይህንን ያህል ብር ነው?" እንበል:: "ስለ ሰረቅሁት እንስሳ ይቅር በለኝ" ከማለት፣ "ትናንት ስለ ሰረቅሁት በግ ይቅር በለኝ" እንበል:: እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ቢያውቀውም እንኳ በፈቃደኝነት ገልጸን በትክክል ንስሐ እንድንገባ ይፈልጋል:: በቃሉም እንዲህ ብሎ ተናግሯል፣ "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም::" (1ኛ ዮሐ. 1:8)::» ለዚህም ስብከታቸው ቄሱ ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ በማለት አስረግጠው ተናገሩ::

«አንድ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ መጥቶ እንዲህ ሲል ንስሐ ገባ:: 'መጋቢ፣ ስለ ኃጢአቴ የመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ አለብኝ፣ ሕሊናዬ ሊያርፍ አልቻለምና ስለሠራሁት በደል እግዚአብሔር ይቅር እንዲለኝ ጸልይልኝ' አለው:: መጋቢውም ደስ ብሎት፣ 'ይህ ዓይነት አቀራረብ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና መልካም ነው:: ለመሆኑ የሠራኸው ኃጢአት ምንድን ነው?' ይለዋል:: አማኙም፣ 'ገመድ ሰርቄአለሁ' ይለዋል:: ይህንንም ኃጢአት መጋቢው በንስሐ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ይጸልይለትና ይለያያሉ:: በሌላ ቀንም፣ በሌሎች ቀናትም፣ እየደጋገመ አማኙ ወደ መጋቢው እየመጣ፣ አሁንም 'የሕሊና እረፍት አጥቻለሁ፣ ኃጢአቴ አላሳረፈኝም፤ እባክህ፣ እንደገና ጸልይልኝ' ይለዋል:: ይጸልይለታል፣ ይሄዳል:: እንደገናም በሌላ ጊዜ ይመጣል:: አንድ ቀን መጋቢው እንዲህ ብሎ ጠየቀው፣ "ይህ ብቻ አይመስለኝምና እስቲ ልጠይቅህ፣ በገመዱ ጫፍ ምን ታሥሮ ነበር?" ቢለው፣ "ፍየል ታስሮበት ነበር" አለው::»

አንባቢ ሆይ፣ እግዚአብሔር አይዘበትበትምና ኃጢአትህን ሳትደብቅ የሠራኸውን ሁሉ አሁኑኑ ተናዘዝ:: ተመልሰህም አትድገመው፣ አቅጣጫህን ቀይር፣ ያን ጊዜ ጽድቅህ እንደ ንጋት ብርሃን ይሆናል፣ የሚቋቋምህም የለም:: ኃጢአት እንዳንሠራ፤ ከሠራንም እውነቱን እንድንናዘዝ መንፈስ ቅዱስ ያግዘን:: አሜን::

ግጥምጥም:- በኃጢአት ተወልደህ በኃጢአት ከምትሞት፣
ኃጢአትህን ተናዘህ ግባ ወደ ገነት::

| |
|---|
| 1ኛ ዮሐ. 1:9-10 |
| ሕዝ. 18:32 |

# በወገቡ የተጠመጠመው እባብ

በየመንደሩ እየዞረ በእባብ እያስፈራራ ትኩስ ወተት መጠጣቱን ቋሚ ሥራ አድርጎታል:: ዛሬ አንዱ ቤት እንደዚህ ያደርጋል፣ ነገ ደግሞ ሌላ ቤት:: ግን ክፉ ልማድ አንድ ቀን ማጥፋቱ አይቀርምና እንደለመደው አንድ ቀን ጠዋት ወደ አንድ መንደር ሄዶ በር ላይ ያገኛትን አንድ ሴት የእባቡን ጭንቅላት ይዞ ወደ እርሷ እያሳየ፣ «ቶሎ ብለሽ ትኩስ ወተት ካላመጣሽ ዛሬ በዚህ እባብ ተነድፈሽ መሞትሽ ነው» አላት:: እርሷም፣ "እሺ" ብላ በድንጋጤ እየተርበተበተች ወደ ውስጥ ገባችና ወተት አምጥታ ሰጠች:: እርሱም ከጠጣ በኋላ ስትርበተበት ስላያት ሴትዮዋን ለማረጋጋት ፈልጎ፣ "አይዞሽ፣ ምን ያርበተብትሻል? ይህ እባብ እንደሆነ አይናደፍም:: ተመልከች" ብሎ በወገቡ የተጠመጠመውን የእባቡን አፍ በአፉ ውስጥ እያስገባ ሲያሳያት ሳያስበው በድንገት እባቡ አፉ ውስጥ በመንደፍ መርዙን ረጭቶ ገደለው::

አዎ፣ ዛሬ ጥቅም ያገኘንበት መስሎን ነገ ሊያጠፋን ያለ ኃጢአት ምን ይሆን? እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣ «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፣ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች፣ እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፣ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እንቢ ብትሉ ግን ብታምፁም፣ ሰይፍ ይበላችኋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና::» (ኢሳ. 1:18-20):: ለዚህ አምላካችን እሺ ብለን በመታዘዝ፣ ኃጢአታችንንም በመናዘዝና በመተው የምድርንም የሰማይንም በረከት እንድንበላ ጌታ ራሱ በጸጋው ይደግፈን:: አሜን::

የቃል ጥናት ጥቅስ: «በደለኞችና ኃጢአተኞች ግን በአንድነት ይሰበራሉ፣ እግዚአብሔርንም የሚተዉ ይጠፋሉ::» (ኢሳ. 1:28)::

ግጥምጥም:- የእባቡን አፍ በአፌ ሕያስተናገድኩኝ፣
ሳላውቀው በድንገት ተቀስፌ አረፍኩኝ::

| |
|---|
| ዮሐ. 8:11 |
| 1ኛ ዮሐ. 1:9 |

# «ኢብራሂም ሰላም ብሎሃል!»

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ» (ኤፌ. 4:25)::

በዚህ ጥቅስ ላይ በመመርኮዝ ሰባኪው የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓመታዊ የአንድነት ፕሮግራም ላይ ለተሰበሰበው ምእመን ትምህርታቸውን እንዲህ እያሉ ቀጠሉ:: «እውነት ያኮራል፣ ያሳድጋል፣ ያለመልማል:: ውሸት ደግሞ በተቃራኒው ያሰድዳል፣ ያዋርዳል:: እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ግን እውነት እየከሳ፣ ውሸት እየወፈረና እየደለበ የመጣ ይመስላል:: እግዚአብሔር ግን ጻድቅ ፈራጅ ነውና እውነት ይክሳ እንጂ ያሸንፋል:: እናንተ በእውነተኛው የእግዚአብሔር ስም የዳናችሁና የተጠራችሁ ሕዝቦች ሆይ፣ እርስ በርሳችሁ እውነትን ተነጋገሩ፣ ተጫወቱ፤ ውሸትን ከሕይወታችሁ፣ ከቤተ ክርስቲያናችሁ፣ ከቤታችሁ አስወግዱ፤ የእውነት ምንጩ እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ ስለ እውነት ልጆቹን ያከብራል:: የውሸት አባትና ምንጩ ሰይጣን ነው:: ሰይጣን ደግሞ ከመጀመሪያ የተዋረደ ስለሆነ ያዋርዳል፤ እርሱን ካዱት» ለሚለው ጠንካራና መሠረታዊ የሆነ ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ::

«አንድ በጌታ የምወደው ባልንጀራዬ በልጅነቱ ውሸት እንዴት አድርጎ በሰዎች ፊት እንዳዋረደው ያጫወተኝን ልንገራችሁ:: አባቱ ልጆቻቸው በጥሩ ሥነ ምግባር አድገው ሥራቸው ለቤተሰባቸው አልፎም ለአገር እንዲተርፍ፣ ጥሩ ዜጋ እንዲወጣቸው፣ በዋልጌነትና በዋዛ ፈዛዛ ዕድሜያቸውን እንዳያሳልፉ የጠበቀ ቁጥጥር ያደርጉባቸው ነበር:: ከዚህ የተነሣ አባታቸውን ይፈራሉ:: በተቻለ መጠን የአባታቸውን ፈቃድ ለመፈጸም ይጥራሉ:: ሆኖም ሁልጊዜ አይሞላምና አንድ ቀን ይህ ጓደኛዬ ከጓደኞቹ ጋር ውጭ አምሽቶ ዘወትር ከሚገባበት ሰዓት በጣም አሳልፎ መጣ:: የቤቱ በር ላይም ቆም ብሎ የአባቱን ነገር አሰላሰለ:: "ምን ይሻለኛል? ልግባ አልግባ" እያለ ተጨነቀ:: በመግባቱም ቆረጠና በር አንኳኳ:: እንደፈራውም በሩን ከውስጥ የከፈቱት እኚያ በጣም የሚፈራቸው አባቱ ነበሩ:: ፊት ለፊት ተፋጠጡ:: ከዚያም የሚለው ግራ ቢገባው በተንተባተበ አንደበት ድንገት በአፉ የመጡለትን የአጎቱን ስም ጠራና፣ "ኢብራሂም ሰላም ብሎሃል፤ አሁን በቀጥታ ከእርሳቸው ጋር ቆይቼ ነው የመጣሁት" ሲል

እጃቸውን በአፋቸው ይዘው፣ ስለ እርሱም አፍረውለት በሩን ለቀቁለት:: ወደ ውስጥ ሲገባ አጎቱ ኢብራሂም ለካ ቀደም ብለው በጊዜ መጥተው ኖሯልና እቤት አገኛቸው:: ከዚያች ሰዓት ጀምሮ አይናገር አይጋገር አንገቱን በእፍረት አቀርቅሮ አመሸ::»

አዎ፣ ክርስቲያኖች፣ ውሸት ያዋርዳል፣ አንገትም ያስደፋል፣ ያሰቅቃልም:: ስለዚህ ይህን አዋራጅ ኃጢአት አስወግደን በየቀኑ ከባልንጀሮቻችን ጋር፣ ከቤተሰቦቻችን ጋር፣ ከጎረቤቶቻችንና ከመንግሥታችን ጋር እውነትን እንድንነጋገር የእውነት አምላክ ራሱ በእውነቱና በጸጋው ይደግፈን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ውሸትን ተሞልተህ ከምትገደረደር፣

እውነትን ተናግረህ ከመሸበት እደር::

| |
|---|
| ዮሐ. 8:31 |
| ዘፍጥ. 39:11-18 |

# ጾም ጸሎት

የቃል ጥናት ጥቅስ «አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል» (ኤፌ. 5:14)::

ሰባኪው፣ «በዚህ ጨለማ ዓለም ውስጥ ብርሃንና ጨው ሆነን መመላለስ የምንችለው ነቅተን በጸሎት ሕይወታችን ስንተጋ ነው:: ዛሬ ሰይጣን ከተያያዘው የውጊያ ስልቱ አንዱ እንቅልፋምና ሰነፍ ማድረግ ነው:: የጨለማ ሥራው እንዳይገለጥ የብርሃንን ልጆች በእንቅልፍ አዚም ይመታልና አሳቡን ሳንስተው ተግተን ልንጸልይና ልንቃወመው ይገባል:: የእግዚአብሔር ቃል እንደሚል፣ "እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፣ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" (ያዕቆብ 5:16):: እርግጥ ነው የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ ኃይለኛን ነገር ታደርጋለች:: ይህንን የተረዳ ሰይጣን በሥራዋ ሥራው እንዳይፈርስበት የጸሎት ትጋታችንን ለማስጣል በጌታ ፊት ተንበርክከን ከመጸለይ ይልቅ ቆመን እንድንጣላ በዘዴ ሥራ ሰጥቶናልና ነቅተን ልንቃወመው ያስፈልጋል:: እስቲ ከዚህ መልእክቴ ጋር የሚሄድ አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ» ብለው ሰባኪው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

«ቤተ ክርስቲያኒቱ ባወጀችው መሠረት ዕለቱ የጾምና ጸሎት ቀን ነው:: ሁሉም በዚያ ቀን ከእህል ውኃ ተቆጥቦ ስለ ግል ሕይወቱ፣ ስለ ቤተሰቡ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኑና ስለ አገሩ በእግዚአብሔር ፊት ያነባል:: በርእስ ተከፋፍሎ በተሰጣቸው መሠረት በየተራ ሰዎች ፕሮግራሙን በጸሎት መምራት ቀጥለዋል:: የቻለ በተንበረከከበት ቆይቶ፤ ያልቻለ ደግሞ እየቆመ ለዕለቱ የተያዘው ሰዓት ሲደርስ ሁሉም በአንድ ላይ ጸልዮ ከጨረሰ በኋላ ፕሮግራሙ አልቆ ሁሉም በየቤቱ ሄደ:: አንዲት ሴት ለካ ጠዋት እንንበርከክ በተባለ ጊዜ የተንበረከከች ፕሮግራሙም ካለቀ በኋላ እንቅልፍ ወስዷት ኖራልና ሳትነቃ ቀረች:: እንቅልፏን ጨርሳ ከተንበረከከችበት ወንበር ስትነሣ ማንም ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የለም:: በዚህ ጊዜ ባደረገችው ነገር ተደናግጣና አፍራ "ሰይጣን፣ ብተኛም በአባቴ ቤት ነው የተኛሁት፣ ደስ አይበልህ" አለች::»

ወገኖቼ፣ በእግዚአብሔር ቤት ሆነን ከተኛን በዓለም ያሉትን ማን ይታደጋቸው? ሰይጣን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ደስ የሚለው በዓለም ሆነን ስንተኛ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቤት ሆነን ስንተኛ ነውና እንንቃ:: ጌታም በቃሉ ያለን፣ «ስለምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ»:: (ሉቃ. 22:46):: በቀረው ዘመናችንም ጌታ የሚተጋ የጸሎት ሕይወትን ያፍስስልን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ሕይወቴ እየሞተ ለምን እተኛለሁ፣
ከእንግዲህስ ይብቃኝ ደጁን እጠናለሁ::

ሉቃ. 22:45

# *የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት*

*«እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደፊት ለምንም አይጠቅምም::»*
*(ማቴዎስ 5:13)*

## የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ ለምን አስፈለገ?

በዚህ ዥንጉርጉር ዓለም ውስጥ ብዙ መፍትሄና ቀና መንገድ የሚጠይቁ ብዙ ዥንጉርጉር ችግሮች መኖራቸው አሌ የማይባል ሐቅ ነው:: በተለይም ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ስንመለስ ይህ ጉዳይ በጣም ጎልቶ ይታያል:: አያሌዎች ለተለያዩ ችግሮቻቸው ምክር በመጠየቅና መልካም የሆነ ምላሽ አግኝተው የሚሄዱበትን ሲፈልጉ እንደ ልብ አያገኙም:: ጥቂቶች ብቻ በጥቂት አማካሪዎች በሚድኸው የማማከር አገልግሎት ምክር አግኝተው ይሄዳሉ:: የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎትም የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ሰዎችን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል በምክር ለማቅናትና ለመደገፍ በእግዚአብሔር ምሪት የተጀመረ የአገልግሎት ክፍል ነው:: /1ኛ ጢሞ. 3:16/

## የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ እንዴት ተጀመረ?

በምክሩ ግሩም የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ይህንን አገልግሎት እንድንጀምር በእኔ እና በባለቤቴ ልብ ራእዩን ሲያመጣ ብዙ ጊዜ በፊቱ የቆይታ ጸሎት አድርገናል፤ ራእዩም ከእርሱ መሆኑን ስናረጋግጥ ሰፊና ትልቅ በሆነው የማማከር አገልግሎት በእርሱ ጸጋ ተደግፈን ጌታ ህዝቡን ለማቅናትና ለመፈወስ በሚሠራበት ዘመን እኛም ከእርሱ ጋር አጠቃላይ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የምክር አገልግሎት በመስጠት አብረን ለመሥራት ወሰንን:: በዚህም መሠረት የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት በ1994 ዓ.ም በነሐሴ ወር ተጀመረ:: /ማቴ. 5:13/

## የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ ግብ ምንድን ነው?.

የጨመማአ ግብ ሰዎች ሁሉ በኀዘንም ሆነ በደስታ ጊዜ ዓይኖቻቸውን ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ላይ ሳያነሡ እንደ እርሱ አሳብ እንዲሄዱና ጌታ በክርስቶስ በኩል ያዘጋጀውን ዘላለማዊ የድኅነት መንግሥት እንዲወርሱ ለመርዳት ነው::

## የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ ዓላማዎች ምንድን ናቸው?.

1. ለሰዎች ሁሉ መልካም ምክር መስጠት፣ ወንጌልን በደብዳቤ መመስከር፣ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎቻቸው ምላሽ መስጠት::
2. ለባለትዳሮችና ትዳር ለሚመሠርቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር መስጠት::
3. አብያተ ክርስትያናትን ለምክር አገልግሎት ለማነሣሣት ትምርትና ሥልጠና መስጠት::
4. መጽሐፍ ቅዱስን በመላላክ መማር ለሚፈልጉ ሁሉ በአድራሻ ማገናኘት::

### የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል::

1. በጋብቻ ዙሪያ:-
   ሀ. ላላገቡ ወጣቶች
   - በትዳር ጓደኛ ምርጫ ዙሪያ
   - በእጮኛሞች ቅድስና ዙሪያ
   - ወጣቶች እንዴት ለጋብቻ ይዘጋጃሉ
   - በቅድመ - ኤች አይ ቪ ምርመራ ዙሪያ
   - በሰርግ ዝግጅት ዙሪያ/ ጥሎሽ፣መልስ፣ቅልቅል/
   - ድንግልና፣እርግዝና፣ውርጃ

   ለ. ላገቡ ባለትዳሮች
   - የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት
   - የቤተሰብ ምጣኔ
   - ኤች አይ ቪ /ኤድስና ባልና ሚስት

- ድርብ ጋብቻ
- ዳግም ጋብቻ
- አገልጋይና ቤተሰቡ
- የልጆች አስተዳደግ
- የወሲብ ችግሮች
- ፍቺ
- ቤተሰብና ጎጂ ባህሎች
- የባልና ሚስት ግንኙነት/ ሚና/

2. ከመጽሐፍ ቅዱስ በሚነሡ ጥያቄዎች ዙሪያ/ መጽሐፍ ቅዱስ ስታነቡ ወይም ስትሰሙ ጥያቄ የፈጠረባችሁ ቢኖር/
3. ኤች አይ ቪ /ኤድስን በተመለከተ ከባለሙያዎች ጋር በመመካከር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር እንሰጣለን።
4. መጽሐፍ ቅዱስን በማስተማርና በመስበክ የሚያገለግሉትን አገልጋዮች ማገልገል፡-
   4.1 በጥያቄዎቻቸው መሠረት ለሚያስተምሩት ትምህርት የሚጠቅማቸውን ምሳሌ በመላክ፣
   4.2 በአገርም ውስጥ ሆነ ከአገር ውጪ መጽሐፍ ቅዱስን በመላላክ መማር ለሚፈልጉ ሁሉ ጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ከሚሰጡ ክፍሎች ጋር ማገናኘት።

እንግዲህ ከላይ በጠቀስናቸው አገልግሎቶች ለመገልገል የምትፈልጉ ሁሉ በቀጣዩ አድራሻችን ጥያቄዎቻችሁን ሁሉ ብትልኩልን ይደርሰናል። እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይባርካችሁ!


አድራሻችን፡- የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት

የመ.ሳ.ቁ. 70893

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ፡- 349-23-57 (የቤት)

091-140-45-54

ኢ-ሜይል፡- sebcm@ethionet.et

ወይም

sebcm2@yahoo.com